# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 234 ሚያዝያ 24 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## «የገበታ ለሀገር ኮይሻ ፕሮጀክት አካል የሆነው ሐላላ ኬላ ሪዞርት ድንቅ የቱሪስት መስህብ ስፍራ ነው»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የገበታ ለአገር ኮይሻ ፕሮጀክት አካል የሆነው ሐላላ ኬላ ሪዞርት ድንቅ የቱሪስት መስህብ ስፍራ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የገበታ ለሀገር ኮይሻ ፕሮጀክት አካል የሆነውን ሐላላ ኬላ ሪዞርት መርቀው ከፍተዋል።

" የገበታ ለሀገር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ከንቲባ አዳነች አቤቤ

## በመዲናዋ በርካታ ፕሮጀክቶች
### የአካባቢውን ፀጋ ታሳቢ አድርገው የተሠሩ ናቸው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በርካታ ፕሮጀክቶች የአካባቢውን ፀጋ ታሳቢ አድርገው የታቀዱና የተሠሩ ናቸው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

የኢትዮጵያ ከንቲባዎች ፎረም ለሁለት ቀናት በአዲስ አበባ ተካሂዷል፡፡ በወቅቱ የተለያዩ ፕሮጀክቶችንም ጎብኝተዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በወቅቱ እንዳስታወቁት፤ በከተማዋ የተገነቡ ፕሮጀክቶች የአካባቢውን ፀጋ ከግምት አስገብቶ የታቀዱና የተሠሩ ናቸው፡፡

በተለይም ኅብረተሰቡን በማሳተፍ የተተገበሩ ድሃ ተኮርና ግዙፍ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜና ጥራት የተጠናቀቁ ናቸው ብለዋል።

የመስቀል አደባባይ፤ የከንቲባ ጽሕፈት ቤት፣ አድዋ ዜሮ ዜሮን ጨምሮ የወዳጅነት ፓርክ ፕሮጀክቶች፣ የአንድነት መኪና ማቆሚያና የአንድነት ፓርክን የመሳሰሉ ሜጋ ፕሮጀክቶች ተገንብተዋል ያሉት ከንቲባዋ፤ የትራፊክ ማኔጅመንት ግንባታ ሂደት፣ አዲስ አፍሪካ የኤግዚቢሽን ኮንቬንሽን ማዕከልና የእንጦጦ ፓርኮችን ሌሎች በመዲናዋ የተሠሩ ግንባታዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የመመገቢያ ማዕከላትና የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ጨምሮ የሥራ ዕድልን በመፍጠር ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮጀክቶች መከናወናቸውን አስረድተዋል፡፡

በመዲናዋ በርካታ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## «የምንመኘው ሰላም ሙሉ በሙሉ እንዲረጋገጥ ከመንግሥት ጋር በጋራ እንሠራለን»

- አቶ ጋትሉዋክ ቡም
የጋምቤላ ነፃነት ግንባር ሊቀመንበር

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- የምንመኘው ሰላም ሙሉ በሙሉ እንዲረጋገጥ ከመንግሥት ጎን በመሆን በጋራ እንሠራለን ሲሉ የጋምቤላ ነፃነት ግንባር (ጋነግ) ሊቀመንበር አቶ ጋትሉዋክ ቡም አስታወቁ፡፡ ከዚህ በኋላ በስማቸው የሚንቀሳቀስ ኃይል አለመኖሩንና በአገሪቱ ሰላም እንዲሰፍን ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታም እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

"የምንመኘው ሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ
### ይበልጥ ለማሳደግ እሴት የተጨመረባቸውን ምርቶች በብዛት መላክ ይገባል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከፍ ለማድረግ ያለውን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም እሴት የተጨመረባቸውን ምርቶች በብዛት ወደውጭ መላክ ይገባል ሲል የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበር ምክርቤት አስታወቀ።

የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## «የመከላከያ ሪፎርም ጠንካራ ኅብረ-ብሔራዊ ሠራዊትን ለመገንባት ትልቅ ዕድል የሰጠ ነው»

- ብርጋዴር ጀኔራል ኃይሉ ጎንፋ

ገጽ 4




# ኢንስቲትዩቱ ለኦዲት ግኝቱ ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራ እንደሚገባ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ለኦዲት ግኝቱ ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራ እንደሚገባ የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰቧል።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በ6ኛው ዙር 2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የእንስሳት ብዝሀ ሕይወት ሀብት አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ የ2014 ክዋኔ ኦዲት መነሻ በማድረግ ውይይት አድርጓል።

የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ወይዘሮ አራሬ ሞሲሳ፣ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የትኩረት አቅጣጫ አድርጎ የተነሳው ኢንስቲትዩቱ የአገሪቱን ብዝሀ ሕይወት ሀብትና ተያያዥ የማህበረሰብ እውቀቶች መጠበቃቸውንና በዘላቂነት ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ላይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የትኩረት አቅጣጫ የኢትዮጵያ ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት አዳዲስ ዘመናዊ አሠራሮችን ተግባራዊ እንዲያደርግ እና ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ውጤታማ የብዝሀ ሕይወት ሀብት አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት እንዲችል መሆኑን የጠቀሱት ምክትል ሰብሳቢዋ፣ አገሪቱ በብዝሀ ሕይወት ተጠቃሚ እንድትሆን ተቋሙ ትኩረት አድርጎ ሊሠራ ይገባል ብለዋል።



ወይዘሮ አራሬ ሞሲሳ



ወይዘሮ መሠረት ዳምጤ

በኢንስቲትዩቱ መሠራት የሚገባቸው ተግባራት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት መሠራት እንደሚኖርባቸው ጠቁመዋል፡፡

ውጤታማ የብዝሀ ሕይወት ሀብት አጠቃቀም እንዲረጋገጥ የብዝሀ ሕይወት ናሙና ከውጭ አገር የሚገቡበት መመሪያ መኖር እንዳለበት አንስተውም፣ በብዝሀ ሕይወት ላይ እየታየ ያለው ክፍተት ያልተጠና በመሆኑ የአወጋገድ ሥርዓት ሊበጅለት እንደሚገባ አሳስበዋል።

በኦዲት ግኝቱ የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የፍቼ ብዝሃ ሕይወት ጅን ባንክ ግንባታ ሳይጠናቀቅ ርክክብ መደረጉ፣ ባልተጠና መንገድ ጉዳት አድራሽ የእንስሳት ዝርያዎችን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት እንዲሁም የእምቦጭ አረምን በዘላቂነት ለማጥፋት ተጨባጭ ሥራዎችን አለመሥራት የመሳሰሉ ጉድለቶች በተቋሙ አፈፃፀም ላይ መስተዋላቸውን ምክትል ሰብሳቢዋ ተናግረዋል፡፡

በተቋሙ ላይ የታየው የኦዲት ግኝት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ እስከ ሚያዝያ 30 ለቋሚ ኮሚቴው፣ ለግብርና ሚኒስቴር እና ለዋና ኦዲተር እንዲቀርብ ያሳሰቡት ሰብሳቢዋ፣ በተጨማሪም የተጀመረው ፖሊሲና መመሪያ እስከ ግንቦት 30 ጸድቆ ሥራ ላይ መዋል እንዳለበትና ለእያንዳንዱ የኦዲት ግኝት ማሻሻያ ተደርጎ በየሦስት ወሩ ሪፖርት እንዲያቀርቡ አሳስበዋል።

የኦዲት ዋና መስሪያ ቤት ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሠረት ዳምጤ በበኩላቸው፣ የብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የተገኙበትን የክዋኔ ኦዲት ጉድለቶች ለማሻሻል ያደረጉት ጥረት አጥጋቢ አለመሆኑን ጠቅሰው፣ ለቁጥጥር አመቺ እንዲሆን የሚልኩት የድርጊት መርሐ ግብር የየሩብ ዓመት መሆን አለበት ብለዋል።



አቶ ውቤ መንግሥቱ

# ኢትዮጵያ ከውጭ አገራት ጋር ያላትን የንግድ ትስስር ለማጠናከር እየተሠራ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከውጭ አገራት ጋር ያላትን የንግድ ትስስር ለማጎልበት እየተሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክርቤት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ አቶ ውቤ መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ የውጭ የንግድ ትስስሯን ለማጎልበት ከ52 አገራት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርማ እየሠራች ትገኛለች፡፡ ከእነዚህ አገራት ጋር የዋጋ መረጃ በመለዋወጥ፣ የንግድ ትርኢቶች ላይ በመገኘትና በመጋበዝ፣ ችግሮችን በጋራ በመፍታትና የልምድ ልውውጦችን በማድረግ የአገሪቱን የውጭ ንግድ ለማሳደግ እየተሠራ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ከውጭ አገራት ጋር ያላትን የንግድ ትስስር ለማጠናከርና ለማስፋት እየሠራች ትገኛለች ያሉት አቶ ውቤ፣ የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በየዓመቱ በአሜሪካ የንግድ አውደ ርዕይ የሚያዘጋጅ ሲሆን ይህም አሜሪካ ላሉ ኢትዮጵያውያን ምርት ለሚያቀርቡ ኩባንያዎች የንግድ ትስስር እንደፈጠረላቸው ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ውቤ ገለጻ፣ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ስምምነት ከፈረመችባቸው ከግማሽ በላይ ከሚሆኑት አገራት ጋር የተሻለና ውጤታማ የንግድ ትስስርን ፈጥራለች፡፡

የውጭ ገበያ ለማግኘት ብዙ ሙከራዎች ተደርገው የሚሳኩ ቢሆንም ትልቁ ችግር ግን በሚፈለገው ልክ ቋሚ ሆኖ ምርት ማቅረብ አለመቻሉ ትስስሩን የሚያላላ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ለዚህም የአቅርቦቱን ችግር ለመፍታት የግል ዘርፉን ማበረታታትና ወደ ሥራ ማስገባት አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ ውቤ በአሁኑ ጊዜ ያለው የውጭ ምንዛሬ እጥረት እና ንግድ ለመጀመር የሚኖረው የመሬት አቅርቦት ችግር ጀማሪ ኩባንያዎችን የማያበረታታ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የምታቀርባቸው ምርቶች አብዛኛዎቹ ከግብርናው ዘርፍ የሚገኙ ቢሆንም የግሉ ዘርፍ ሰፋፊ እርሻ ወይም ሰፋፊ የእንስሳት ልማት በማካሄድ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያበረታታ የአሠራር ሥርዓት አለመዘረጋቱን ነው የተናገሩት፡፡

የአቅርቦት እጥረት ባለባቸው ምርቶች ላይ የግሉ ዘርፍ ትኩረት እንዲሰጥ መንግሥት እያበረታታ መሆኑ የሚያስመሰግነው ቢሆንም አሁን በስፋት ትኩረት ከተሰጠው ከስንዴ ምርት በተጨማሪ ሌሎች ምርቶች ተጠንተው ትኩረት ሊያገኙ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

ከውጭ አገራት በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያን ምርት መግዛት በመለማመድ ሁሉም የራሱን ኃላፊነት እየተወጣ ለትውልድ የሚተላለፍ ነገር መሥራት እንደሚገባ አቶ ውቤ አሳስበዋል፡፡

# በትግራይ የወደሙ ኢንተርፕራይዞችን መልሶ ለማቋቋም እየተሠራ ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

ጅግጅጋ፡- በትግራይ ክልል የሚገኙ የወደሙ ኢንተርፕራይዞችን መልሶ ለማቋቋም እየተሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አስታወቀ።

የኢንተርፕራይዙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ጳውሎስ በርጋ የተቋሙን የዘጠኝ ወራት አፈጻጸም አስመልክቶ እንደተናገሩት፣ እስካሁን በትግራይ ክልል ያለው የኢንተርፕራይዝ ልማት እንቅስቃሴ በእቅድ አልተካተተም ነበር።

በአሁኑ ወቅት ግን መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ትኩረት ተሠጥቶት እየተሠራ ይገኛል። ከዚህ ቀደም በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል ቡድን ተቋቁሞ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል ያሉት አቶ ጳውሎስ፣ በቅርቡም ጥናቱን መሠረት በማድረግ ከክልሉ ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ተካሂዷል ብለዋል። በዚህም አካባቢው በጦርነት የቆየ በመሆኑ በአጭር በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የሚሠሩት ሥራዎች እንደተለዩ ተናግረዋል።

ተመሳሳይ ችግር በአማራ ክልል ገጥሞ የተቀናጀ ድጋፍ ማድረግ መቻሉን ያስታወሱት አቶ ጳውሎስ፣ ያንን ልምድ መሠረት በማድረግ በቅድሚያ በጦርነቱ ከደረሰው ሥነልቦናዊ ቀውስ ለማላቀቅ ስልጠናዎች ይሠጣሉ፤ ለዚህም ከፍተኛ የሥነ ልቦና ባለሙያዎች እየተዘጋጁ ይገኛል ብለዋል።

አቶ ጳውሎስ እንዳሉት፣ ኢንተርፕራይዞቹ ያጋጠማቸው ችግር ዝርዝር ጥናት ተደርጎ ያሉትን ክፍተቶች በመለየት የክልሉ ኢንዱስትሪ ቢሮ ውድመት ስለገጠመው መልሶ ከማቋቋም ጀምሮ የተቀናጀ ድጋፍ ለማድረግ እየተሠራ ነው። ለዚህም በመንግሥትና በኢንዱስትሪ ልማት በኩል በተለየ ሁኔታ ድጋፍ ለማድረግ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል።

ከገንዘብ ሚኒስትርና አጋር የልማት ድርጅቶች ጋር በመሆን ሀብት የማሰባሰብና እቅድ የማዘጋጀት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል ያሉት አቶ ጳውሎስ፣ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ድጋፍ የሚያደርጉበት ሁኔታም የሚመቻች ይሆናል ብለዋል። በቅርቡም ወደ ትግራይ በማቅናት አጠቃላይ ሥራዎች እንደሚጀመሩ ጠቁመው፣ ይህም ሆኖ ለውጤታማነቱ የሚመለከታቸው አካላት ትብብር ያስፈልጋል ብለዋል።

የትግራይ ክልል ኢንዱስትሪ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ መሀሪ ገብረሚካኤል በበኩላቸው ላለፉት ሦስት አመታት በክልሉ ያሉት ኢንተርፕራይዞች ሁሉም በተለያየ ደረጃ ውድመት እንደደረሰባቸው በማስታወስ እስካሁን ሥራ የጀመረ አለመኖሩን ገልጸዋል።

የሠላሙ መፈጠር የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩን ለማጠናከርና የደቀቀውን ኢኮኖሚ እንዲያንሠራራ ለማድረግ በር ይከፍታል ያሉት አቶ መሀሪ፣ ለዚህም ጊዜያዊ አስተዳደሩ አቅጣጫ አስቀምጦ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል። ለዚህም የሦስት ወር እቅድ ተይዞ ወደሥራ የተገባ ሲሆን በዚህ ጊዜም በቅድሚያ የደረሰውን ጉዳት በዝርዝር የመለየት ሥራ ይሠራል ብለዋል።

የደረሰው ውድመት ከፍተኛ በመሆኑም ለክልሉ የሚመጥን መመሪያ ተዘጋጅቶ ዕዳ የሚሠረዝበትና አዳዲስ ብድሮች በፍጥነት ተደራሽ የሚሆኑበት ሁኔታ እንዲመቻች እንፈልጋለን። ደደቢትና ካዛ የሚባሉት ብድር አቅራቢ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማትም የውድመቱ አካል በመሆናቸው እንደአዲስ ሥራ ማስጀመር ይጠበቃል። ለዚህም ከብሔራዊ ባንክና ልማት ባንክ ብዙ ሥራ ይጠበቃል ብለዋል።

አሁን የተሳተፍንበት የዘጠኝ ወር ግምገማ አዳዲስ አሠራሮችና መመሪያዎችን እንዲሁም ክልሎች ያሉበትን ሁኔታ እንድናውቅ ረድቶናል ያሉት አቶ ጳውሎስ፣ በመሆኑም የምንጠብቀው ነገር ከተሟላ በፍጥነት ወደ ሥራ በመግባት ወጣቱን ከስደትና ተደራራቢ ችግር ለመታደግ ያስችለናል ብለዋል።

ከፌዴራል መንግሥት በተጨማሪ ክልሎችም ከዚህ ቀደም በክፉም በደግም አብረን እንደነበርን ሁሉ አሁንም ከጎናችን ሊሆኑ ይገባል ያሉት አቶ መሀሪ እነዚህን ኢንተርፕራይዞች በፍጥነት ወደ ሥራ ማስገባት በዘርፈ ብዙ ችግር ውስጥ ያለውን የትግራይ ሕዝብ መታደግ በመሆኑ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

# በትግራይ ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችን ወደመደበኛ ሥራቸው ለመመለስ እየተሠራ ነው

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል የሚገኙ አራት ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን ተቀብለው ለማስተማር እንቅስቃሴ መጀመራቸውን የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር የአስተዳደርና መሠረተ ልማት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር ሰለሞን አብርሃ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በክልሉ የሚገኙ አራት ዩኒቨርሲቲዎች በጦርነቱ ምክንያት የደረሰባቸውን ጉዳት ከመጠገን ጎን ለጎን ተማሪዎችን ተቀብለው ለማስተማር እንቅስቃሴ ጀምረዋል፡፡

በተጨማሪም በጦርነቱ ምክንያት ወደ ሌላ የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በመግባት ትምህርታቸውን መከታተል ያልቻሉ የትግራይ ክልል ተማሪዎችን የማካካሻ ትምህርት ለመስጠት እንቅስቃሴ መጀመሩን ያብራሩት ዶክተር ሰለሞን፣ ይህ መርሃ ግብር ከክልሉ ተወላጆች ውጪ በትግራይ ክልል ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩና ወደ ሌሎች የአገሪቷ ዩኒቨርሲቲዎች ተመድበው ትምህርታቸውን መቀጠል ያልቻሉትን እንደሚያጠቃልል ተናግረዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲዎቹ ላይ የደረሰውን ጉዳት የመጠገንና አስፈላጊውን የመሠረተ ልማት የማሟላት ተግባር ከመማር ማስተማር ጎን ለጎን ይካሄዳል ሲሉ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ጠቁመዋል፡፡

ከጦርነቱ በፊት በመደበኛ፣ በቀንና በማታ ትምህርታቸውን፣ በቅድመ፣ በድህረና በሦስተኛ ዲግሪ መርሃ ግብር ሲማሩ የነበሩ ተማሪዎች ለማስተማር ምዝገባ መጀመሩንም ተናግረዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎቹ በፍጥነት ተጠግነው ወደ ነበሩበት የመማር ማስተማር አገልግሎታቸው እንዲመለሱ ትምህርት ሚኒስቴር አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ዶክተር ሰለሞን ገልጸዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲዎች ተመድበው መደበኛ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩ ከ20 ሺህ በላይ ተማሪዎችንና ተመራቂዎችን ጨምሮ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በመመደብ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ የማድረግ ሥራ መሠራቱን አስታውሰው፣ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር እንቅስቃሴ ከመጀመሩም በተጨማሪ ለዩኒቨርሲቲዎች ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋልም ብለዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎቹ ሙሉ ለሙሉ ተማሪ ተቀብለው አገልግሎት እንዲሰጡ ትምህርት ሚኒስቴር በልዩ ትኩረት እየሠራ ነው ያሉት ኃላፊው፣ ዩኒቨርሲቲዎቹ ማስተማር በሙሉ አቅም እንዲጀምሩ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና የአካባቢው ኅብረተሰብ እየሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር ድጋፍና ክትትል ከሚያደርገው በተጨማሪ የሚመለከተው አካል የቻለውን በማድረግና ዩኒቨርሲቲዎች የደረሰባቸውን ጉዳት መልሶ በመገንባት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

በጦርነቱ ምክንያት በዩኒቨርሲቲዎች የደረሰው ጉዳት ጥናት የሚያስፈልገው በመሆኑ የቀጣይ 12ኛ ክፍል አገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና የሚወስዱ ተፈታኝ ተማሪዎችን መቀበል አለመቀበሉን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር እንደሚገለጽ አመላክተዋል፡፡

ዜና



አቶ ግርማ ገመቹ

# በክልሉ 35 በመቶ የፕላስቲክ ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ምርት ከደረጃ በታች ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ የፕላስቲክ ከረጢት አምራች ፋብሪካዎች ላይ በተደረገ ቁጥጥር 35 በመቶዎቹ የሚያመርቱት ፕላስቲክ ከደረጃ በታች መሆኑን የኢፌዴሪ አካባቢ ባለስልጣን አስታወቀ።

የኢፌዴሪ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ሕግ ተከባሪነት ዳይሬክተር አቶ ግርማ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ሰበታ፣ ቡራዩ እና ሱሉልታ ከተሞች ላይ የተለያዩ ፕላስቲክ ከረጢት ውጤቶችን አምርተው ለገበያ የሚያቀርቡ ሃያ ሰባት የፕላስቲክ አምራች ተቋማት ላይ ክትትል ተደርጓል።

በማምረቻ ድርጅቶቹ ላይ በተደረገው ቁጥጥር 94 የናሙና ልኬት ተደርጎ፤ 33ቱ ሕግ ከሚፈቅደው 0.03ሚሊ. ሜትር እና በታች ውፍረት ያለው ምርት የሚያመርቱ ናቸው። በዚህም ቁጥጥር ከተደረገባቸው ፋብሪካዎች 35 በመቶዎቹ ሕግ የማያከብሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ መቻሉን አብራርተዋል።

አምራች ድርጅቶቹ የሚጠቀሙት የምርት ግብዓት በዝርዝር የተለየ ሲሆን፤ አሮጌ የፕላስቲክ ውጤቶች፣ በጣም ቀላል ክብደት ያላቸው /high density polyethylene or HDPE/ ከፍተኛ እፍግታ ያለው ፖሊ ኢትሊን ኬሚካል እና በክብደታቸው ከፍ የሚሉ /low density polyethylene or LDPE/ አነስተኛ እፍግታ ያላቸው ፖሊ ኢትሊን ኬሚካል የተቋማቱ ዋንኛ የምርት ግብዓቶች ናቸው ብለዋል።

የፕላስቲክ ከረጢት እና መጠቅለያ አምራቾች ከሚጠቀሟቸው ግብዓቶች ለመረዳት እንደሚቻለው ሃያ ሰባቱ የፕላስቲክ አምራቾች በስብሶ ከአፈር የማይዋሃድ የፕላስቲክ ከረጢት እና መጠቅለያ የሚያመርቱ መሆናቸውን ገልጸዋል።

እንደ አገር ውፍረታቸው 0.03 ሚሊሜትር እና በታች ሆኖ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይዋሃድ የፕላስቲክ ከረጢትን ማምረትም ይሁን ከውጭ አገር ማስገባት የተከለከለ በመሆኑ የፕላስቲክ ውጤቶችን አምርተው ለገበያ የሚያቀርቡ ድርጅቶች ላይ ክትትል ተደርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ግርማ ገለጻ፣ በተከታታይ ዓመታት በከተሞቹ ከተደረጉ የቁጥጥር ውጤቶች ለመረዳት እንደተቻለው በቡራዩ ከተማ ስምንት ድርጅቶች፤ በሰበታ ከተማ ደግሞ ሰባት ድርጅቶች ከዘርፉ የወጡ ሲሆኑ፤ በአጠቃላይ አምራች ተቋማት እና የሚያመርቱት ሕገ ወጥ የፕላስቲክ ከረጢት እና ማሸጊያ መጠን እና ዓይነት እያደገ ይገኛል። ይህም የሚደረገው ክትትል እና ቁጥጥር እንዲሁም ሕግ በማያከብሩ ተቋማት ላይ የሚወሰደው ሕጋዊ እና አስተዳደራዊ ርምጃ እየላላ የሄደ መሆኑን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ፋብሪካዎቹ ሕግ በሚፈቅደው እንዲያመርቱ ለማድረግ የኦሮሚያ ክልል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እና የከተማ አስተዳደሮች የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤቶች የሚደረገውን ቁጥጥር የሚያጠናክሩበት ስልት አዘጋጅተው መተግበር ይኖርባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል።

በተጨማሪም ከደረጃ በታች የሆነ የፕላስቲክ ከረጢት እና መጠቅለያ እያመረቱ በተገኙ አምራቾች ላይ አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባም አሳስበዋል።

በአምራቾች ላይ አተኩሮ እየተሠራ ያለው የቁጥጥር ሥራ ብቻውን ተገቢ ውጤት የሚያመጣ ባለመሆኑ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በዋና ዋና አከፋፋዮች ላይ የቁጥጥር ሥራ በመሥራት የሕግ ማዕቀፋንም በዚህ ታሳቢነት ማሻሻል እንደሚገባ አስረድተዋል።

# የይርጋዓለም አጠቃላይ ሆስፒታል የኩላሊት እጥበት ማዕከል ሥራ ሊጀምር ነው

**አምሳሉ ፈለቀ**

ይርጋለም፡- የይርጋዓለም አጠቃላይ ሆስፒታል የኩላሊት እጥበት ማዕከል ሥራ ለማስጀመር የቅድመ ዝግጅት ሥራ እያጠናቀቀ መሆኑን አስታወቀ፡፡

የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ አቶ ተመስገን ሳርሚሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሆስፒታሉ የኩላሊት እጥበት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ማዕከል ግንባታ በማጠናቀቅ በቅርቡ ወደ ሥራ ይገባል፡፡

የኩላሊት እጥበት ማዕከሉ በግንባታ ደረጃ መሠረታዊ ነገሮችን አሟልቷል ያሉት አቶ ተመስገን፤ ለዚህም አስፈላጊ የሆኑ ሰባት ማሽኖች ከጀርመን አገር እንዲገባ መደረጉን ተናግረዋል፡፡

ሆስፒታሉ በአዲስ መልክ ሊጀምር ያቀደውን ይህንን የኩላሊት እጥበት ማዕከል ሥራ ሊያስጀምር የሚችል ከጤና ሚኒስቴርና ከጳውሎስ ሆስፒታል የተውጣጣ የባለሙያዎች ቡድን አጠቃላይ ሂደቱን ድጋፍና ክትትል እያደረገ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

በማዕከሉ የኩላሊት በሽታ ተጠቂዎች የቅድመ ጥንቃቄ አገልግሎት ለሚስፈልጋቸው ሰዎች በቀጣይ ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱን ለማስጀመር ዕቅድ የተያዘ ሲሆን፤ በበሽታው በጠና ለታመሙት ደግሞ ቀጥሎ ባሉት ጊዜያት ሙሉ የእጥበት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዷልም ብለዋል፤ ሥራ አስኪያጁ፡፡

ወደ ማዕከሉ ከገቡት ሰባቱ ማሽኖችም በቀጣይ ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ አራቱን ማሽኖች ወደ ሥራ በማስገባት በቀን በአማካይ ለ12 ሰው አገልግሎቱን ለመስጠት እና በሂደትም ሙሉ በሙሉ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ እየተሠራ እንደሆነም ተጠቁሟል፡፡

የይርጋዓለም ሆስፒታል በቅርቡ የሚያስጀምረው የኩላሊት እጥበት አገልግሎት መስጫ ማዕከሉ ተንቀሳቅሰው መታከም ለሚችሉና በጤንነት እጦት ምክንያት ህመም ለጠናባቸውና በራሳቸው መንቀሳቀስ ለማይችሉ እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች ለመንቀሳቀስ ምቹ እንዲሆን ታስቦ የተገነባ ሲሆን፤ ተላላፊ የሆኑ ህመሞች



ላሉባቸውና ዲያሌሲስ ለሚያስፈልጋቸው ደግሞ የተለየ ክፍል ተዘጋጅቶላቸዋልም ነው ያሉት አቶ ተመስገን።

በኩላሊት ጽኑ ህክምና ላይ ሳሉ እጥበት ለሚያስፈልጋቸውም እንዲሁ በተለየ ሁኔታ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን፤ በሰባቱም ማሽኖች እንደየህመሙ ደረጃ ለሚገኙ ታካሚዎች አስፈላጊው የእጥበት አገልግሎትን በተሟላ መልኩ እንደሚሰጥም ተናግረዋል፡፡

የኩላሊት እጥበት ህክምና ውድ ከሆኑ ህክምናዎች አንዱ ሲሆን ለዚህም መነሻው ለማሽኖቹ ጥቅም ላይ የሚውሉት ከውጭ በዶላር የሚገቡ ምርቶች በመሆናቸው ነው ያሉት አቶ ተመስገን፤ በዚህኛው ማዕከል ግን ለተገልጋይ አመቺ በሆነና የታካሚዎችን የክፍያ አቅም በማይጎዳ ሁኔታ አገልግሎትን መሠረት ባደረገ መልኩ እንደሚሠራም ነው የጠቆሙት፡፡

በማዕከሉ ለታካሚዎች ተገቢውን አገልግሎት መስጠት የሚችሉ በዘርፉ የሰለጠኑ ብቁ የህክምና ባለሙያዎችን ከማፍራት አኳያም ከጤና ሚኒስቴርና ከጳውሎስ ሆስፒታል ጋር በመቀናጀት ከማሽኑ ጋር በተያያዘና ሌሎችም ተያያዥ ሙያዎች በተለያየ ጊዜና ሁኔታ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ አስፈላጊውን ስልጠና የወሰዱና በመውሰድ ላይ የሚገኙ እንዳሉም ታውቋል፡፡

አያይዘውም በቀጣይ በማዕከሉ የሚሰጠው አገልግሎት እንዳለ ሆኖ የኩላሊት በሽታ በባህሪይው ምልክት ሳያሳይ የሚያጠቃ በመሆኑ አብዛኞቹ ሰዎች በሽታው ከጠናባቸው በኋላ ነቅተው ወደ ህክምና ስለሚሄዱና ከዚያ በኋላም ለመመለስ አዳጋች ስለሚሆን እጥበትን እንደ አማራጭ እንደሚወሰድ የጠቆሙት አቶ ተመስገን፤ ሰዎች ግን የጤናቸውን ሁኔታ ለማወቅ ለኩላሊት ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ጊዜ መሠረታዊውን የጤና ምርመራ ማድረግ እንዳለባቸው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ከውጭ አገር ሥራ ስምሪት ከ40 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከውጭ አገር የሥራ ስምሪት ከ40 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል እንደገለጹት፤ በአለፉት ዘጠኝ ወራት ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉና የመዳረሻ አገራትን የሚያሰፉ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡

በተሠሩት ሥራዎች አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ የወጣቶችን ተጠቃሚነት በማሳደግ ረገድም ሆነ የመዳረሻ አገራትን በማስፋት ዙሪያ የተሠሩት ሥራዎች ውጤት እያስመዘገቡ መሆናቸውን አብነት አንስተው አስረድተዋል፡፡

ከ56 ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጎች በሕጋዊ መንገድ የሥራ ስምሪት ተጠቃሚ መሆናቸውን አንስተው፤ ኤጀንሲዎች በተለያዩ አገራት ካሰማሯቸው ዜጎች ሁለት ነጥብ 11 ቢሊዮን ብር ወይም ከ40 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ገቢ ስለመገኘቱ ክትትል ተደርጓል ብለዋል፡፡ የተገኘው ገቢም ከዕቅዱ አንፃር ሲታይ 60 በመቶ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የውጭ የሥራ ስምሪት መዳረሻ አገራትን ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትሯ፤ እስካሁን ለሕጋዊ የሥራ ስምሪት ስምምነት የተደረገባቸው አገራት ቁጥር አራት መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

ከጆርዳን፣ ኳታር፣ የተባበሩት አረብ ኤሚሬትስ እና ሳዑዲ አረቢያ ጋር የሥራ ስምምነት መደረጉን ጠቅሰውም፤ ሌሎች አገራትም ፍላጎት እያሳዩ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ወደ ውጭ አገራት ለሥራ ስምሪት የሚላኩት ዜጎች በከፊልና ሙሉ በሙሉ የሰለጠኑ መሆናቸውንና አገራቱ



ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል

በሚያቀርቡት የፍላጎት መረጃ መሠረት እየተላኩ እንዳለ አብራርተዋል፡፡

የዜጎች ክብር ተጠብቆ የሥራ ስምሪት ማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መፈጠሩን አንስተው፤ የሥራ ስምሪት የሚያከናውኑ ኤጀንሲዎች ላይ ከፍተኛ ክትትል እና ቁጥጥር እየተካሄደ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ሙፈሪያት ገለፃ፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ሪፖርት ላላቀረቡ 27 ኤጀንሲዎች የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡ በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ሪፖርት ለማስገባት ፈቃደኛ በማይሆኑ ኤጀንሲዎች ላይም የመጨረሻ ደረጃ እርምጃ ለመውሰድ ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

# «የመከላከያ ሪፎርም ጠንካራ ኅብረ-ብሔራዊ ሠራዊትን ለመገንባት ትልቅ ዕድል የሰጠ ነው»

**- ብርጋዴር ጀኔራል ኃይሉ ጎንፋ**

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- አዲሱ የመከላከያ ሪፎርም ከብቃት ባሻገር የሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ውክልና እንዲኖር በማድረግ ጠንካራ ኅብረብሔራዊ ሠራዊት ለመገንባት ትልቅ ዕድል የሰጠ መሆኑን የቀድሞ የሠራዊቱ አመራርና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ብርጋዴር ጀኔራል ኃይሉ ጎንፋ ገለጹ። የክልሎች ልዩ ኃይል እንደገና ማደራጀት ተገቢና ወቅታዊ መሆኑንም ተናግረዋል።

ብርጋዴር ጀኔራል ኃይሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ ከዚህ ቀደም በስም የአገር መከላከያ ሠራዊት ቢባልም በተግባር ግን ፍጹም የአንድ ወገን የበላይነት የሰፈነበት ተቋም ነበር፤ በሠራዊቱ ውስጥ የውክልና ጉዳይ የሚታሰብ አልነበረም። በአዲሱ ሪፎርም ግን ብቃት ያለው የሁሉንም ብሔር ተወካይ በማሳተፍ ኢትዮጵያን የሚመስልና የሚመጥን መከላከያ እየተገነባ መሆኑን መገንዘባቸውን ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ መከላከያ በስብጥሩ፣ በአመለካከቱና በብቃቱ ኢትዮጵያን በይበልጥ የሚያኮራ ሠራዊት መሆኑን እርግጠኛ ነኝ ያሉት ብርጋዴል ጀኔራል ኃይሉ፤ ውትድርና ብቃት ብቻ ሳይሆን በቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በትምህርት ደረጃና በዘመናዊ የውትድርና ጥበቡ የተሻለ መከላከያ ሠራዊት እየተገነባ ነው ብለዋል።

ሆኖም ግን የውትድርና እውቀትን ከፖለቲካ አመለካከታቸው ጋር በማዛመድ ጀግናውን የአገር መከላከያ ሠራዊት ለማጣጣል የሚፈልጉ ፖለቲከኞች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማየትና መስማት የተለመደ ክስተት ሆኗል ያሉት ብርጋዴር ጀኔራሉ፤ ዳሩ ግን መከላከያ ሠራዊት ባይኖር አገር የሚባል ነገር እንደማይኖር የዓለም እውነታ መሆኑን በማጤን የመከላከያ አደረጃጀት፣ መርሆና ቁመናን ካለማወቅ የሚወረወር ትችት መቆም እንዳለበት አሳስበዋል።

እንደ ብርጋዴር ጀኔራል ኃይሉ ማብራሪያ፣ መከላከያ ሠራዊት የአንድ አገር የመጨረሻ ምሽግ በመሆኑ አንድ ወታደር ወደ መከላከያ ሲቀላቀል አገራዊ እይታ እንዲኖረው ማድረግ ወታደራዊ ግዴታ ነው። መከላከያ እንዴት፣ በማን፣መቼና ምን ግዳጅ መፈጸም እንዳለበት በጥብቅ ዲስፕሊንና መመሪያ የሚመራ ተቋም እንጂ በፖለቲከኞች ጫጫታና ጩኸት የሚመራና የሚዘወር ስብስብ አይደለም። ዓላማውም በችግር ጊዜ ከአገር በፊት ራሱን ማስቀደም ነው።

በተለይ በአሁኑ ጊዜ በሚስተጋባው የአፍራሽ ኃይሎች ጫጫታ መከላከያ አገራዊ እይታ ባይኖረው መዘዙ ቀላል አይሆንም ነበር ያሉት ብርጋዴር ጀኔራሉ፤ ከለውጡ ወዲህ የሰሜኑ ጦርነትና የአልሸባብ ትንኮሳ አገራዊ እይታ ያለውና ብቁ አገር መከላከያ ባይኖር ኖሮ ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት አይከብድም ብለዋል። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ መከላከያ ብቃትና ቁመና አስተማማኝ ደረጃ ላይ መሆኑን ዓለም የመሰከረው ጉዳይ እንደሆነም ጠቁመዋል።

በአሁኑ ጊዜ የአገር መከላከያ ሠራዊት በሪፎርም ጭምር እየታገዘ እየተጠናከረ መምጣቱን የገለጹት ብርጋዴር ጀኔራል ኃይሉ፤ የልዩ ኃይል አደረጃጀቱ የመከላከያን ስብጥርና ብቃት ከማሳደጉም በተጨማሪ አገራዊ እይታን በሚሸረሽር መልኩ በክልሎች መካከል የሚስተዋለውን አላስፈላጊ ፉክክር ያስቀራል ብለዋል።

# «የገበታ ለሀገር ኮይሻ ፕሮጀክት አካል...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ባደረጉት ንግግር፣ በጊቤ ሦስት የኃይል ማመንጫ አማካኝነት ከተፈጠረው ሰው ሠራሽ ሐይቅ ዳርቻ የሚገኘው የሐላላ ካብ በ’ገበታ ለሀገር’ ኮይሻ ኮሪደር ፕሮጀክት አካል በሆነው ሐላላ ኬላ ሪዞርት ውስጥ ተካቶ የለማ ድንቅ የቱሪስት መስህብ ስፍራ መሆኑን ተናግረዋል።

ሐላላ ኬላ ሪዞርት ከመዝናኛ ስፍራነቱ በተጨማሪ ታሪካዊና ባህላዊ ሙዚየሞችና የምርምር ማዕከላትን ያካተተ መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኘው የዳውሮ ዞን ለዓይን የሚማርኩ መልከዓ ምድር፣ ታሪካዊና ባህላዊ መስህቦች ባለቤት ስለመሆኑም አንስተዋል።

ኢትዮጵያውያን ለብዙ ሥራዎች አእምሯችሁ እንዲከፈት የሕዝብና አካባቢ ሰላም በእጅጉ በሚገኝበት የዳውሮ ዞን በመምጣት አዳዲስ ሀሳቦችን ለማፍለቅና ውስጣዊ ሰላም ለማግኘት የገበታ ለሀገር ኮይሻ ፕሮጀክት አካል የሆነውን ሐላላ ኬላ ሪዞርት እንዲጎበኙም ጥሪ አድርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሸትን በማለባበስ እውነት ማድረግ እንደማይቻልና ውሸትን ቀባብቶ እውነት ለማስመሰል መሞከር እንደ ሐላላ ኬላ ያሉ ፕሮጀክቶችን ለመፍጠር አያስችልም ሲሉም አክለዋል።

ኢትዮጵያ ህብረ ብሔራዊት የብዙ ባህልና ቋንቋዎች መገኛ አገር ናት ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ይህንን ብዝኃነት እንደራስ መቀበልን መለማመድ ያስፈልጋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ህብረ ብሔራዊ አገር ናት የምንለው በባህልና ቋንቋ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮም እጅግ ማራኪ ሕብረ ብሔራዊ ቀለማትን በውስጧ የያዘች አገር መሆኗን መረዳት ያስፈልጋል፤ በዚህም አንዱ አካባቢ ከሌላው የተለየ የራሱ ተፈጥሯዊ ገፀ በረከቶችን የያዘ በመሆኑ በአግባቡ በማልማት መጠቀም እንደሚገባ አጽንዖት ሰጥተው ተናግረዋል።

በመጨረሻም የዳውሮ ማህበረሰብ የሐላላ ኬላ ሪዞርት እንደቀደሙ አባቶች ቅርስ በመጠበቅ ለትውልድ እንዲያሸጋግርና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱን እንዲያረጋግጥ አሳስበዋል።

ሐላላ ኬላ ሪዞርት ዓለም አቀፍ የቱሪስት መዳረሻ ደረጃዎችን አሟልቶ የተገነባ እንደሆነ በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የተገኙ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች ገልጸዋል።

የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች በክላስተር ተከፋፍሎ በተሠራው የሐላላ ኬላ ሪዞርት ፕሮጀክት የልማት ሥራው አካባቢዎች ካላቸው ተፈጥሯዊ ጸጋዎች ጋር ተጣጥሞ መከናወኑ አካባቢውን ይበልጥ ሳቢ እንዳደረገው በምርቃት ወቅት ተናግረዋል።

የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር እርስቱ ይርዳው ሐላላ ኬላ ሪዞርት የመሠረት ድንጋይ ሲቀመጥ አካባቢው በደቡብ ክልል ስር የነበረ መሆኑን አስታውሰው፣ አሁን ደግሞ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል አካል ሆኖ በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ መገኘታቸው ልዩ ስሜት እንደፈጠረባቸው ተናግረዋል።

ከሐላላ ኬላ ታሪካዊ መስህብ በተጨማሪ የዳውሮ ዞን በባህል ዘርፍም ማራኪ ጸጋዎችን የተላበሰ መሆኑን የገለጹት ደግሞ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሽመልስ አብዲሳ ናቸው።

ከሦስት ዓመታት በፊት ከአካባቢው ማህበረሰበብ ውጪ ይህንን ስፍራ ብዙዎች ያውቁታል የሚል እምነት እንደሌላቸው የገለጹት ርዕሰ መስተዳድር ሽመልስ አሁን ለምረቃ የበቃው ሐላላ ኬላ ሪዞርት እንደ አገር ትልቅ የቱሪዝም አቅም የተፈጠረበት ስፍራ ነው ብለዋል።

የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሙስጠፌ መሀመድ በበኩላቸው፣ እንደ ቱሪዝም ያሉ መስኮች ተፈላጊውን አገራዊ ጠቀሜታ እንዳይሰጡ ወደ ኋላ ከሚጎትቱ ጉዳዮች መካከል የሰላም እጦት አንዱ መሆኑን ገልጸው፤ የገበታ ለሀገር ኮይሻ ፕሮጀክት አንድ አካል የሆነው ሐላላ ኬላ ሪዞርት ቱሪዝም ዋና የገቢ ምንጭ መሆኑን ያሳየ ፕሮጀክት ሆኖ ማግኘታቸውን ተናግረዋል።

በተመሳሳይ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር ጌታቸው ረዳ፣ ሐላላ ኬላን ለመጀመሪያ ጊዜ የተመለከቱት የሰላም ስምምነቱን ለመገምገም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር የተገናኙበትን ታሪካዊ ዕለት በመጥቀስ አሁን ግን ሪዞርቱ በተሟላ መልኩ ተጠናቅቆ መመልከታቸውን በበጎ እንደተመለከቱት ገልጸዋል።

የቱሪዝም ፕሮጀክቶችን ማስፋት ካለው ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አንጻር እያንዳንዱ ዜጋ አገሪቱ ያላትን አቅም በመረዳት የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ጥሪ ቀርቧል።

# «የምንመኘው ሰላም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የጋነግ ሊቀመንበር አቶ ጋትሉዋክ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ እንደ አንድ ሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ ብሎም ለሰላም እንደሚተጋ ድርጅት ለሰላም መደረግ ያለበትን ሥራ ሁሉ ለመሥራት ዝግጁ ናቸው፡፡ ሰላም ሙሉ በሙሉ እስኪረጋገጥ ድረስም ከመንግሥት ጎን በመሆን በጋራ ለመሥራት ተዘጋጅተዋል፡፡

እንደ ዜጋ ሲታይ ለሰላም የተቻለኝን ሁሉ ለማበርከት ግዴታ እንዳለብኝ ይሰማኛል ያሉት አቶ ጋትሉዋክ፤ ስለዚህም በየአገሪቱ ሰላም እንዲሰፍን ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር አለብን፡፡ ስለሰላም ሲባል ከመንግሥት ጎን በመሆን እንሠራለን የሚል አቋም የያዝነውም ለዚህ ነው ብለዋል፡፡

የሰላም መንገድ ለመከተል እስከመጣን ድረስ ከክልሉ መንግሥት ጋር ለመሥራት ያሰብነው ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ነው ሲሉም ጠቅሰው፤ በተለይም ከክልል መንግሥት ጋር በሚጋሩ ጉዳዮች ላይ መሥራት የሚጠበቅባቸውን በጋራ እና በአንድነት ለመሥራት መወሰናቸውን አመልክተዋል፡፡

አቶ ጋትሉዋክ፤ ከሰላም ብዙ ማትረፍ ይቻላል በሚል መንፈስ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ለማካሔድ እስከተስማማን ድረስ የክልሉ የሰላም ጉዳይ ይመለከተናል ሲሉም ተናግረዋል፡፡ ክልሉ ሰላም ሆነ ማለት የሁላችንም ሰላም የሚጠበቅና ልማቱም እድገቱም የሚመጣ በመሆኑ በአብሮነት መሥራቱ ተገቢ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

እርሳቸው እንዳሉት፤ የሚነሱ የእኩልነትም ሆኑ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ቢኖሩ በጋራ በመሥራት የተሻለ እድገት በማስመዝገብ መመለስ ይቻላል፡፡ ይህ ሲሆን በአገር ደረጃም ሆነ በክልል ደረጃ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ከፍ ያለ ሚና ይኖረዋል፡፡

‹‹እኛ በተደረገልን የሰላም ጥሪ መሠረት አገር ውስጥ ገብተናል፡፡ ይሁንና አንግበን የነበሩ ጥያቄዎች ገና አልተመለሱም፡፡ ቢሆንም የእኛ አመለካከት በመጀመሪያ ለሰላም ቅድሚያ እንስጥ የሚል ነው፡፡ ምክንያቱም ሰላም ከሁሉ መቅደም ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ሰላም በሌለበት የማንንም ሙብት ለማክበር ያስቸግራል፡፡ ጥያቄ ለማስመለስም ሆነ በጋራ ለመልማት የሚቻለው ሰላም ሲኖር ነው፡፡›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ይህ ሰላም የሚመጣው ደግሞ በአንድ አካል ብቻ በሚደረግ ጥረት ሳይሆን በጋራ ነው ያሉት አቶ ጋትሉዋክ፣ እነርሱም ይህን በመገንዘብ የሰላሙ አካል ለመሆን ፈቅደው ትጥቅ መፍታታቸውን አስረድተዋል፡፡

በቀጣይም የእኛ አስተዋጽኦ የሚሆነው በመንግሥት የተያዙ ትልልቅ አጀንዳዎች ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው አቅማችን በፈቀደው ሁሉ በጋራ መሥራት ነው፡፡ ልማቱ ለአገራችን የሚደረግ ሥራ እስከሆነ ድረስ እኛም የዚሁ ተጠቃሚዎች ነንና የቻልነውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁዎች ነን ብለዋል፡፡

በጋምቤላ ነፃነት ግንባር ስም ካሁን በኋላ ታጥቆ የሚንቀሳቀስ ኃይል አለመኖሩንና በሰላማዊ መንገድ ለመቀንቀሳቀስ ወደ ጋምቤላ መመለሳቸውን የግባሩን ሊቀመንበር ሰሞኑን ይፋ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡

# የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከሚያዝያ 18-22 ቀን 2015 ዓ.ም ሲካሄድ የቆየው 13ኛው የኢትዮ- ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ተጠናቋል።

በመዝጊያ መርሃ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክርቤት ፕሬዚዳንት ኢንጂነር መላኩ እዘዘው እንደገለፁት፤ ኢትዮጵያ በርካታ ተፈጥሯዊ ሀብቶች ቢኖሯትም ለበርካታ ያደጉ አገራት እሴት ከተጨመረባቸው ምርቶች ይልቅ በብዛት ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ሆና ቆይታለች።

በአገራችን ያለውን የግብርና፣ የማዕድን፣ የእንስሳት፣ የደን፣ የቱሪዝም እና የሰው ሀብት ወደ ኢኮኖሚ ዕድል በመቀየር ዘላቂ ገቢ መፍጠር እንችላለን ብለዋል።

እንደ ኢንጂነር መላኩ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ጥሬ ዕቃ ብቻ አቅራቢ ሆና መቀጠል የለባትም የሚል የፀና አቋም መያዝ ይገባል። የግል ዘርፉ የሚያመርታቸውን ምርቶች እሴት ጨምሮ በማቅረብ ወደ አገር የሚገባውን የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ ይኖርበታል።

ያለንን ተፈጥሯዊ ሀብት እሴት እየጨመርን ለውጭ አገር የመላኩ ሥራ ተጠናክሮ ቢቀጥል ኢኮኖሚያችንን ከፍ ለማድረግ ያስችለናል ያሉት ኢንጂነር መላኩ፤ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከፍ ለማድረግ ያሉንን አንፃራዊ ሀብቶች ልንጠቀም ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽኑ ሲዘጋጅ የኢትዮጵያን ይግዙ በሚል መሪ የተነሳንበት ዋነኛው ምክንያት አሁን ላይ የምናመርታቸው ምርቶች በጥራትም ሆነ በዋጋ ደረጃ ከውጭ ከሚገቡት ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማሰብ ነው ያሉት ኢንጂነር መላኩ አምራቾች ምርቶቻቸውን በዓለምአቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ መሥራት እንደሚጠበቅባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

ኢትዮጵያ ከግብርና ምርቶች ወጪ ንግድ የምታገኘው በአመት ከአራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር የበለጠ አይደለም፤ ነገር ግን ከ18 እስከ 20 ቢሊዮን ዶላል ዋጋ ያላቸው ምርቶችን ታስገባለች ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በቀጣይ ምርቶችን በብዛትና በጥራት በመላክ በወጪና በገቢ ንግድ መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ አምራቾች ጠንካራ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

የኢትዮጵያን ይግዙ በሚል መሪ ሀሳብ ሲካሄድ የቆየውን 13ኛው የኢትዮ ቻምበር ዓለምአቀፍ የንግድ ትርዒት የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክርቤት ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመተባበር አዘጋጅተውታል። በመዝጊያ በመርሃ ግብሩም ለንግድ ትርዒቱ መሳካት የበኩላቸውን ላበረከቱ አካላት የዕውቅና መርሀግብር ተካሂዷል።

# በመዲናዋ በርካታ ፕሮጀክቶች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የድሃ ተኮር ፕሮጀክቶችን ያስጎበኙት ከንቲባዋ 240 አባወራዎችን ተጠቃሚ ያደረገውን የጋራ መኖሪያ ቤትና የለሚ ኩራ የምገባ ማዕከል በምሳሌነት የሚጠቀሱ ፕሮጀክቶች መሆናቸውን ተናግረዋል።

በዕለቱ የተመረቀው የለሚ እንጀራ መጋገሪያና ምርት ማዘጋጃ ማዕከል ለ4 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን ገልጸዋል፡፡

ከንቲባዎች በቀጣይ በተቀናጀ መልኩ በጋራ መሥራት አለብን ያሉት ወይዘሮ አዳነች፤ የከንቲባዎች ፎረም ለመማማርና ለመነጋገር ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ገልጸዋል፡፡

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው እንዳስታወቁት፤ በአዲስ አበባ የተከናወኑ ሥራዎች ሌሎች ከተሞች ምሳሌ የሚሆኑ ናቸው።

ፕሮጀክቶቹ የትውልድ አመለካከትን፣ የሥነ ልቦና ግንባታንና የይቻላል መንፈስን ያሳዩ ናቸው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ፕሮጀክቶቹ በሌሎችም ከተሞች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ልምድ የተወሰደባቸው መሆኑን ጠቁመዋል።

የሌሎች ከተሞች ከንቲባዎች ፕሮጀክቶችን እንዴት መምራት እንደሚቻል ልምድ እንዳገኙ ሚኒስትሯ ገልጸዋል።

የኢኮኖሚ ዕድገት፤ ከተሜነትና ብልጽግና አይቀሬ ጉዳዮች መሆናቸውን ጠቁመው፤ በአሁኑ ጊዜ ለከተሞች የተሰጠው ትኩረት አበረታች ነው፡፡ በዚህም በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች ለውጦች ይታያሉ ብለዋል።

ሚኒስትሯ እንዳስታወቁት፤ ከተሞች በዕድገት ደረጃ፣ በአስተዳደር ሁኔታቸውና በሕዝብ መጠናቸው እንቅስቃሴዎች መሻሻሎች እየታየባቸው ይገኛል። በመዲናዋ የተዘጋጀው የከንቲባዎች ፎረም የእርስ በእርስ ግንኙነቱን በማጠናከር የሚረዳ ልምድ የተገኘበት ነው።

በኢትዮጵያ የሚገኙ 300 የክልል አመራሮችና የከተማ ከንቲባዎች ለሁለት ቀናት በአዲስ አበባ የተገነቡ የልማት ሥራዎችን ጎብኝተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከሰላም፣ ከእርቅና ይቅርታ ትርፍ እንጂ ኪሳራ የለም!

ለአንድ አገር ልማትና ዕድገት ሰላም ከምንም በላይ የገዘፈ ዋጋ አለው። ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት ነው፣ የሰላም ዋጋ በምንም አይነት ምድራዊ ዋጋ አይሰላም፤ ተመንም ሆነ መስፈሪያ እንዲሁም ማንፀሪያ የለውም። የአገርና የሕዝብ ሰላም ትልቅ ዋጋ አለው፣ ሰላም ለአገር ልማትና እድገት ዋነኛው ምሰሶና መሰረት ነው።

ሰላም የሰውን ልጅ የአዕምሮ እና የልብ መረጋጋት፤ ከሚያስጨንቁ ነገሮች ነፃ መሆን ብሎም በአጠቃላይ የሰው ልጅ ውስጣዊና ውጫዊ እረፍት ማግኘት ነው። ለዚህም ነው ሰላማችን ይበዛ ዘንድ ሁላችንም ለአገራችን ሰላም ዘብ መቆም አለብን የሚባለው።

የኢትዮጵያ መንግሥት በተደጋጋሚ ለሰላም ሲል ብዙ ነገሮችን ሲያልፍ እና በይቅርታ ለመሻገር ሲደክም እና ረጅም ርቀት ሲጓዝ እንደነበር የማይካድ ሃቅ ነው። ዛሬም ይሄን ጥረቱን አጠናክሮ እንደቀጠለ ለማንም የተደበቀ አይደለም።

ላለፉት ሁለት ዓመታት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተፈጠረው ችግር እልባት ያገኘው በድርድር ሂደት መሆኑ ከግጭት በኋላ የሚገኘው ሰላም ዘለቄታ እንዲኖረው አድርጓል። በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በመንግስት እና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት ባለፉት ሁለት ዓመታት የተፈጠሩትን ጫናዎች የሚያስወግድ ስምምነት መሆን ችሏል።

ከስምምነቱ ኢትዮጵያ ብዙ አትርፋለች። በስምምነቱ የሠላም ወጋገን መፈንጠቅ ጀምሯል። የሰላም ስምምነቱ ትሩፋት ግን በዚህ ብቻ የሚገለጽ አይደለም። በስምምነቱ ማግስት ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ማትረፍ የቻሉባቸው በርካታ መስኮች ተስተውለዋልና።

መንግስት የነበረው ደም አፋሳሽ ጦርነት እንዲቆም በማድረግ ሕዝብ የሰላም አየር እንዲተነፍስ ሆደ ሰፊ ሆኖ የተጓዘበት ርቀት የሚደነቅ ነው። ሰሞኑን ከሸኔ ጋር በታንዛኒያ የጀመረው የሰላም ውይይትም የሕዝብን ሰላም ከመመለስ ባሻገር ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ የመፍታት ዘላቂ የሆነ የመወያየት ባህል መሰረት እንደሚሆን አርቆ ማሰብ ያስፈልጋል።

እውነተኛ እና ዘላቂነት ያለው ሰላም የሚገኘው ክፉውን በመልካም አሸንፈን እንጂ በክፉ መልሰን አይደለም። በአገራችን ተከስቶ ሕዝባችንን ዋጋ ያስከፈለውን ግጭት በሰላም መንገድ በአግባቡ አርመን ወደ ዘላቂ ሰላም ካልተመለስን የኢትዮጵያን የብልጽግና ጉዞ ማሳካት አንችልም።

"እርቅ ደም ያድርቅ" እንዲሉ የእርቅን ጥቅም በመቀበል ወደ ተሻለ ነገር ለመራመድ ሕዝቡን ከሚከፋፍሉ ነገሮች መቆጠብ ለኢትዮጵያ ከምን ጊዜውም በላይ አስፈላጊ ነው። ማንኛውም ግለሰብ ከማናቸውም አደረጃጀት ነፃ አድርጎ የሰላም ጥሪን በማሰማት ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ሰላም መረጋገጥ ለሰላም በሰላም መስራት መጣር እና ለውጥ ማምጣት ለነገ የሚቆይ የቤት ስራ አይደለም።

ማንኛውም ዜጋ ሰላም እና አንድነትን ለማረጋገጥ ጉልበትን ሀብትን እንዲሁም ስልጣንም ሆነ ነጠላ እውቀትን እንደ አማራጭ መውሰድን አቁሞ የተከሰቱብንን ችግሮች በውይይት እና በድርድር በመፍታት በጦርነት በረሃብና በድርቅ የተጎዱ ወገኖቻችንን የምንታደግበት ትልቅ እድል በእጃችን ይገኛልና እንጠቀምበት።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ "በጦርነት የረጅም ዘመን ታሪክ ያላት ኢትዮጵያ የጦርነትን አውዳሚነት ሩቅ ሳትሄድ ካለፉት ሁለት ዓመታት ብዙ ተምራለች" ብለዋል። ግጭት በህይወት የመኖር የተቃርኖ ዕውነታ ቢሆንም ለሰው ልጆች ሰላም ሲባል በአዎንታ የሚደገፍ አይደለም። ዓለማችን በተለያዩ ዘመናት በርካታ ግጭቶችን አስተናግዳለች እያስተናገደችም ትገኛለች። እንዲያም ሆኖ ከግጭቶች በኋላ የሚገኘው ሰላም ዘለቄታ እንዲኖረው ለማድረግ ሲባል ግጭቶችን በሰላማዊ ንግግር እና ድርድር መፍታት አዋጭ ስለመሆኑ ተደጋግሞ የታየ ሀቅ ነው። በርካታ የታሪክ ድርሳናት የሚነግሩንም በዓለማችን ላይ የተከሰቱ አብዛኞቹ ግጭቶች እና አለመግባባቶች መቋጫ መንገድ ንግግር እና ድርድር ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ነው።

በመሆኑ መንግስት ለየትኛውም አካል የሚዘረጋው የሰላም እጅ ትርፍ እንጂ ኪሳራ የለውምና ከሕዝብ ድጋፍ ሊቸረው ይገባል። መንግስት ለሰላም እጁን የዘረጋው የኢትዮጵያንና የሕዝቧን ዘላቂ ጥቅም ለማስከበር መሆኑንንም በሚገባ መገንዘብ ይገባል።

የአገርን ብሔራዊ ጥቅም ሰላምና ደኅንነት መጠበቅ፣ የተጀመሩ የልማት ስራዎችን ማስቀጠልና ለውጤት ማብቃትም የመንግስት ብቻ ሳይሆን የሕዝቡም የጋራ አገራዊ ኃላፊነትና ግዴታ ነው። ለዚህም ሲባል ከአገር ሰላም በፊት የሚቀድም ሌላ ምንም ጉዳይ አይኖርም!

**አዲስ ዘመን**
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የተሳከሩ ተቃርኖዎችን ማስታረቅ - ለኢትዮጵያ ሰላም

አሸብር ኃይሉ

ምድር ላይ ህይወት እስካለ ድረስ ፍጥረታት በሙሉ ኑሯቸው በተቃርኖዎች ታጅቦ እና ታጅሎ እንዲኖሩ ይገደዳሉ። ምክንያቱም ተቃርኖዎች ተፈጥሯዊ ስለሆኑ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ታዋቂው የማርክሲዝም ፈላስፋ ሄግልም ተቃርኖን «Everything inherently contradictory » ሲል ገልጸዋል።

ተቃርኖዎች በሰዎች ብቻ የሚፈጠሩ የሚመስለን በርካቶች ነን። ይህ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ ተቃርኖዎች የሚፈጠሩት በተፈጥሮ ነውና። ይሁንና ተፈጥሮ ያመጣቻቸውን ተቃርኖዎች የምንፈታበት ዘዴ እና ጥብብ ግን የሰዎችን የአስተሳሰብ ደረጃ አጉልቶ ሊያሳየን ይችላል።

በነገራችን ላይ በመላው ዓለም የሚታዩ እድገቶች በሙሉ የተቃርኖ ውጤቶች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም ለአንድ አገር ሁለንተናዊ እድገት ለማስቀጠል የተቃርኖዎች መኖር የግዴታ ነው። ነገር ግን ምን አይነት ተቃርኖ ? የሚለውን መለየት ያስፈልጋል።

የተቃርኖ መነሻቸው እና አይነታቸው በጣም በርካታ በመሆናቸው የተቃርኖ አይነቶችን አንድ፤ ሁለት ብለን መዘርዘር አንችልም። ይሁንና ጠቅለል አድርገን ስንመለከት ተቃርኖዎችን የተሳከሩ (ጤናማ ያልሆኑ) እና ጤናማ ብለን በሁለት ልንከፍላቸው እንችላልን። ይህ የራሴ አስተሳሰብ ነው። የፖለቲከኞች ወይም የፈላስፎች ያሉት አይደለም።

ጤናማ ተቃርኖዎች የአንድን አገር ሁለንተናዊ እድገት ያፋጥናሉ። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በመላው ዓለም የሚታዩ እድገቶች በሙሉ የተቃርኖ ውጤቶች ናቸውና። በአንጻሩ ተቃርኖዎች የተሳከሩ እንደሆነ ደግሞ የሚያስከትሉት ችግርም እጅጉን ሰቅጣጭ ይሆናል።

በዓለማችን በተለያዩ አገራት በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሰረት ያደረጉ ደም አፋሳሽ ግጭቶች ውስጠ ምክንያታቸው የተሳከሩ ተቃርኖ ስለመሆናቸው ማንም የሚረዳው ነው።

ለአብነት ያህል የሩቆቹን ትተን በቅርብ በሶሪያ፣ በየመን፣ በሊቢያ እና በደቡብ ሱዳን እንዲሁም ከሰሞኑ በሱዳን የተከሰቱ ግጭቶችን መንስኤ ስንመለከት በቡድኖች መካከል የሚፈጠሩ ጤናማ ያልሆነ ወይም የተሳከረ ተቃርኖ ነው። በእኛ አገርም በተለይ በሰሜኑ ክፍል ተከስቶ የነበረው ጦርነት ዋና ምክንያት የተሳከረ ተቃርኖ የወለደውን መሆኑን የሚያጠራጥር አይደለም።

የተሳከረ ተቃርኖ ሲያጋጥም «በሰጥቶ መቀበል » መርህ በሰከነ መልኩ ተቃርኖዎችን ማስታረቅ ይገባል። ምክንያቱም በተሳከረ ተቃርኖ ሳቢያ በሰው ህይወት መልሶ መተካት አይቻልምና፤ በንብረት ላይ የሚያስከትለው ውድመት ለመተካት በርካታ የጉልበት እና የገንዘብ ወጭዎችን ይጠይቃልና። ይህም አንድን አገር እድገት ክፉኛ ወደ ኋላ ይጎትተዋል።

የተሳከሩ ተቃርኖዎችን በግብዝነትም ወይም ግብታዊነት (spontanus) ለመፍታት መሞከር ያልቦካ ሊጥን ምጣድ ላይ አፍስሶ እንደማነኮር የሚቆጠር ነው። የአልቦካ ሊጥ ምጣድ ላይ ማፍሰስ አንደኛ ጉልበታችንን ያባክናል። ሁለተኛ ኢኮኖሚያችንንም ይጎዳል። ስለዚህ ጥሩ እንጀራ ለመጋገር መጀመሪያ ሊጡ መቡካት ይጠበቅበታል። ምጣድ ስላለን ብቻ ግን ያልቦካን ሊጥ እንጀራ ማድረግ አይቻልም። ምክንያቱም ሁሉም ነገር ስርዓት አለውና።

ከጉልበት ይልቅ ውይይት ተቃርኖዎችን ለማስታረቅ ሁነኛ መፍትሄ ተደርጎ መወሰድ አለበት። ሁሌም ቢሆን የተሳከሩ ተቃርኖዎችን በውይይት እንጂ በጉልበት ለመፍታት መሞከር ትርፉ ኪሳራ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ከሰሞኑ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ተከስቶ የነበረውን ችግር የተፈታበት እና ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የተሄደበት እርቀት ደግሞ የጤናማ ተቃርኖ ውጤት መሆኑን ለመረዳት የሚከብድ አይደለም።

የሚገርመው በዚህ ጤናማ በሆነ ተቃርኖ ውስጥ ስለምን ሰላም ወረደ ? በሚመስል መልኩ የተሳከረ ተቃርኖ ያንጸባረቁ ኃይላት በርካቶች መሆናቸው ተመለከትኩ። በእርግጥ ብዙ አልተገረምኩም! ምክንያቱም በኢትዮጵያ ዘመናዊ የፖለቲካ ታሪክ በተለይም ደግሞ ከጣሊያን ዳግም ወረራ በኋላ የተፈጠሩ ፖለቲከኞች አብዛኞዎቹ በኢትዮጵያ መጥፋት ላይ የራሳቸውን ኪስ ለማደለብ የሚንቀሳቀሱ ስለሆኑ። ከሰሞኑ የነበረውን ጤናማ ተቃርኖ ተመልክተው ሂስ ለመስጠት የሞከሩትም እነዚህ በህዝቦች ግጭት ትርፍ የሚያጋብሱ ኃይላት ናቸው።

የሚገርመው እነዚህ ኃይላት አብዛኛዎቹ ዲያሌክታዊ (DIALECTICS) አስተሳሰብ አራማጅ ነን ይላሉ። በተግባር ግን ዲያሌክታዊ አስተሳሰብን ሲያራምዱ አልተመለከትናቸውም። ምክንያቱም ዲያሌክታዊ (DIALECTICS) አስተሳሰብ የሚያራምዱ ሰዎች ነገሮችን በመመርምር በጥልቀት የሚከራከሩ እና የሚወያዩ፤ በክርክራቸው እና በውይይታቸውም የነገሮችን እውነተኛ መዳረሻ መርምረው የሚያገኙ ናቸው። ዲያሌክታዊ ማለትም ይህ ስለሆነ።

ፈላስፎች እንዲህ ይላሉ" አይነ ስውር ያለ መሪ ሩቅ መንገድ ለመሄድ ይቸገራል። ለመሄድ ቢሞክር ብዙ ጉዳቶች ይደርሱበታል"

ከሰሞኑ የተፈጠረውን የሰላም ስምምነት ያልተዋጠላቸው ኃይሎችም ከራሳቸው ውጭ ማንንም የማያደምጡ ግብዞች መሆናቸውን ከቀደመ ታሪካቸው መገንዘብ ይቻላል።

በነገራችን ላይ ከሰሞኑ በአገራችን የተሳከሩ ተቃርኖዎችን ለማስወገድ የተሄደበት እርቀት እጅግ የሚደነቅ እና ይበል የሚያሰኝ ነው። የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ «ጦርነት ይብቃ ሰላምን እናጽና» በሚል መሪቃል ከሰሞኑ በወዳጅነት አደባባይ በተካሄደው ውይይት የተለያዩ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት እንደገለጹት፤ ሁለቱ ጎራዎች ሰላምን ለማምጣት የሄዱበትን እርቀት እውቅና ሰጥተው እና አመስግነዋል፤ የስምምነቱ አተገባበርም በፕሪቶሪያው ስምምነት መሰረት መፈፀም እንዳለበት አጽኖት ሰጥው ሲናገሩ ሰምተናል።

እውነት ነው ! የሰላም አተገባበር ሂደቱ የፕሪቶሪያውን ስምምነት መሰረት ያደረገ መሆን ይገባዋል። ከዚህ በተጨማሪ አፈጻጸሙ በታሰበው ልክ እንዲሄድ የሚደረጉ ማናቸውም ዓይነት እንቅስቃሴዎች መቶ በመቶ ግብታዊነት (spontanus) የጸዱ መሆን አለባቸው።

ግብታዊነትን ትርጉም ለመረዳት መጀመሪያ ንቃተ ህሊና የሚለውን መረዳት ያስፈልጋል። ሰዎች የታሪክን አመጣጥ ተረድተው፤ የህብረተሰብን ህግጋቶች ተከትለው እንዲሄድ ሲያደርጉ ንቃተ ህሊናቸው ዳብሯል ይባላል። ነገር ግን ታሪክን በዘፈቀደ እንደአመጣጡ እየተረጎሙ እና የአንድን ማህበራዊ ህጎች እየጣሱ ለመሄድ መሞከር ግብታዊ አካሄድ ይባላል።

ከዚህ አንጻር ስምምነቱን በፕሪቶሪያው ስምምነት መሰረት ለማድረግ የኢትዮጵያዊውን ሁለንተናዊ ማህበራዊ ህግጋቶችን በደንብ መረዳት ከህግጋቶቹ አንጻር አፈጻጸሞቹን ቅኝታቸውን የተስተካከለ ማደረግ ያስፈልጋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን የአገራችንን ሁለንተናዊ እድገት ለማፋጠን ከፈለግን ለከዚህ በኋላ የሚኖሩን ተቃርኖዎች ጤናማ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ እያንዳንዱ ዜጋ እንደዚህ ቀደሙ በዘፈቀደ በግብታዊነት (spontanus) ከሚደረጉ ንግግሮች እና ውሳኔዎች ሊታረም ይገባል።

እውነታው ሳይጠፋን ለፖለቲካ ጥቅም ሲባል ብቻ ታቀርኖዎችን እንዲሳከሩ ማድረግ ያስከፈለንን ዋጋ የሚታወቅ ነው። ከሰሞኑ የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ «ጦርነት ይብቃ ሰላምን እናጽና» በሚል መሪቃል የተከናወኑ አይነት ጤናማ ተቃርኖዎች የአገረ መንግስቱን ስለሚያጸና ስለሆነ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊደግፈው ይገባል ባይ ነኝ ። ሰላም !

# ነፃ ሀሳብ

## የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪ ቃል “ጦርነት ይብቃ፤ ሰላምን እናጽና!!!”

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ባለፈው እሁድ (ሚያዝያ 15) የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ተራማጅ እሳቤ እውን ያደረገ የምስጋናና የአብሮነት መርሀ ግብር ተካሂዷል። “ጦርነት ይብቃ ሰላምን እናጽና” በሚል መሪ ቃል የሰሜን ኢትዮጵያን ጦርነት በሰላም እና በንግግር እንዲቋጭ ላደረጉ አካላት በወዳጅነት አደባባይ የምስጋናና የእውቅና ስነስርአት እውን ሆኗል።

በስነስርዐቱ ላይ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እና የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የተገኙ ሲሆን፤ የአፍሪካ ህብረት ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ መሀመድ፣ የናይጀሪያው የቀድሞ ፕሬዚዳንትና የአፍሪካ ህብረት የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ ኦሊሴንጎ ኦባሳንጆ፣ የቀድሞው የኬኒያ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ፣ አምባሳደር ማይክ ሀመር፣ የኢጋድ ሊቀመንበር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁ እንዲሁም የክልል ርዕስ መስተዳድሮች እና ሌሎች እንግዶችም የስነስርዐቱ አካል ነበሩ።

በዝግጅቱ ላይ ያለፈችውንና አሁን ያለችውን ኢትዮጵያ እያነጻጸሩ የተለያዩ እንግዶች ንግግር አድርገዋል። ከሰላም በኋላና ከሰላም በፊት የነበረችውን ሁለት መልክ ኢትዮጵያ እያስታወሱ የሰላምን ዋጋ በማግነን የጦርነትን እሳቤ በመኮነን ስለአንድነት የተሰሙ ድምጾች እልፍ ነበሩ።

ከነዚህ የሰላም አዋጅ ድምጾች ውስጥ አንዱ የቀድሞው የኬኒያ ፕሬዚዳንት የኡሁሩ ኬንያታ ንግግር አንዱ ነው። በንግግራቸው “ኢትዮጵያውያን በሰላምና በአንድነት የቆየና የነበረ አብሮነታቸውን እንዲቀጥሉ፣ የአንድነትና የወንድማማችነት መንፈሳቸውን አጠናክረው በተሻለ ሊተጉ ይገባል” ሲሉ ተናግረዋል።

እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት የአቶ ጌታቸው ረዳ ንግግር ነው። ርዕሰ መስተዳደሩ የነበረውን የጦርነት ጊዜ በማስታወስ “የትግራይ ህዝብ ጦርነት ሰልችቶታል፣ አንገሽግሾታል” ያሉ ሲሆን ከዚህ ጋር የሚዛመድ የሰላም፣ የአንድነትና የእርቅ ድምጻቸውን አሰምተዋል።

ርእሰ መስተዳድሩ “ከትግራይ ህዝብ ይዤ የመጣሁት የሰላምና የፍቅር መልዕክት ብቻ ነው” ያሉ ሲሆን “ሁሉንም ነገር ሰላም መር በሆነ እሳቤ እናድርገው። ከጎረቤት ህዝቦች፣ ከአማራና ከአፋር ጋር ሊያጋጨን የሚገባ ነገር ሳይኖር አብሮነታችንን በሰላም ማስቀጠል ለምንፈልገው ሰላም የላቀ ዋጋ አለው” ሲሉ ተደምጠዋል።

ከዚህ ጋር አያይዘው ለአራት ዓመት ያክል ትምህርት ያልጀመሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተማሪዎች በክልላችን ያሉ ሲሆን የእኔን ቤተሰብ ጨምሮ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ተፈናቃዮች አሉን። በቀጣይ እነዚህ ነገሮች ተስተካክለው ሰላማችን ሙሉ እንዲሆን ሁላችንም መረባረብ አለብን ብለዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን በመርሀ ግብሩ ላይ ለሰላም አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት የምስጋና ሽልማት የተሰጠ ሲሆን በቀጣይም ኢትዮጵያ ከነሙሉ ሰላሟ ጸንታ እስክትቆም ድረስ የአጋር አገራት ትብብር ይቀጥላል ሲሉ በስነስርዐቱ ላይ የተገኙት የውጪ አገራት ዜጎች ተናግረዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የሰላም ሂደቱን የበለጠ ለማጠንከርና አስተማማኝ ለማድረግ በታቀደ ሀሳብ መሰረት በቀጣይ ሳምንት በብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት የተመራ የልኡክ ቡድን ወደ መቀሌ እንደሚያቀና የተናገሩ ሲሆን፤ የልኡክ ቡድኑ የሁሉንም የክልሎች ርዕሰ መስተዳድሮችን ያካተተ እንደሚሆንም ጠቁመዋል።

ለሰላም የምንችለውን ሁሉ በማድረግ አገር እንፈጥራለን ያለው የጠቅላይ ሚኒስትሩ መልዕክት ካሳለፍነው ተምረን መጪውን የተሻለ ለማድረግ በሁሉም ረገድ ተግባቦት የታከለበት ርምጃ እየወሰድን እንገኛለን ብለዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የተጀመረውን የሰላም ጉዞ ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግ ሌላ የሰላም ዜናም አብስረዋል።

“የኢትዮጵያ መንግስት ከሸኔ፣ ወይም ደግሞ ራሱን ’የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት’ እያለ ከሚጠራው ታጣቂ ቡድን ጋር ከነገ በስቲያ በታንዛኒያ ድርድር እንደሚጀምር” ገልጸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አያይዘውም “በዚህ ድርድር ላይ የሚሳተፉ ወገኖች የዛሬዋን ቀን እያሰቡ፣ ከግጭት፣ ከጦርነት እንደማናተርፍ አውቀው ህግ እና ስርዐትን በተከተለ መንገድ ይቅር ተባብለን አገራችንን በጋራ ማነጽ እና መገንባት እንድንችል እና የወለጋ ህዝብ አሁን ካለበት ስቃይ እፎይ ማለት እንዲችል ሁሉም ወገኖች የበኩላቸውን እንዲያደርጉ ከወዲሁ ጥሪዬን አቀርባለው” ብለዋል።

ከዚህ እውነት በመነሳት አገራችን ለሰላም ያላትን ቁርጠኝነት መረዳት ይቻላል። የሰላም እጦት በሁሉም መስክ ዋጋ ሲያስከፍለን መቆየቱ የአደባባይ ሀቅ ቢሆንም ልዩነታችንን አቻችለን በእርቅና በተግባቦት ወደፊት መቀጠል ተስኖን ነበር። በዚህ ሰላምን በኃይል ለማምጣት በመሞከር እሳቤ ውስጥ ብዙ ዋጋዎችን ከፍለን ዛሬ ላይ በሰላምና በእርቅ ለምስጋና ቆመናል።

የትኛው እንደሚበጀን አይጠፋንም። የጠፋን በመነጋገርና በላቀ የሀሳብ የበላይነት ተነጋግሮ መግባባት ነው። ሰው የሚስተው ባልገባውና ባልተረዳው ነገር ላይ ነው። የእኛ ስህተት ግን ባወቅነውና በተለማመድነው እውነት ላይ ነው። ጦርነት ለዘመናት መገለጫችን ሆኖ እንደቆየ እናውቃለን።

በጦርነት ብዙ የሞትና የአካል መጉደል ስብራቶችን እንዳስተናገድን እናውቃለን። ይሄ ሳይበቃን በድህነት ላይ ቁምጥና ሆኖብን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ ህይወታችን ምን ያክል ኪሳራ እንዳደረሰብን የአደባባይ ሀቅ ነው። ይሄን ሁሉ እውነት ይዘን ለዳግም ስህተት ወደ ጦርነት መግባታችን ለሰሚው ግራ ከመሆኑም በተጨማሪ አቻ የሌለው የስህተትና የአለማወቅ አባዜ ነው።

ሰው ከወንድሞቹ ጋር ይረዳዳል፤ ይተባበራል እንጂ ከወንድሞቹ ጋር ጦርነት አይገጥምም። በአገራችን እንዲህ ያለውን ነውር የሚያወግዝ፤ “ወንድሙን ታግሎ የጣለ ጀግና አይባልም” የሚል ብሂል አለ።

እነዚህን መሳይ አስተማሪ ተረቶች የተነገሩት በአባቶቻችን አንድነትና ወንድማማችነት ላይ ተመስርተው ነው። እኛም በተግባራቸው ላይ ቆመን ሰላሳና ስልሳ መቶም አፍርተን ድህነትን “ምን አባክ” ማለት ሲገባንና ልማትና ብልፅግናን ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ ስንችል የተሰጠንን የአንድነትና የአብሮነት ስነቃል በእኔነት ለመሻር እየተንፈራገጥን እንገናኛለን።

የአባቶቻችን የሆነ ሁሉ ውብ ነው። ያለፉበትን፣ ያሸነፉበትን፣ ጽናትና ልዕልናን ያገኙበትን ምስጢራቸውን ነው የሰጡን። እንዴት በአንድነት አገር እንደሰሩ፣ እንዴት ብለው ወራሪውን ፋሽስት አሳፍረው እንደመለሱ፣ እንዴት ብለው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን እንዳቆዩልን በስነ ቃል አማካኝነት አስተላልፈውልናል።

እንዴት ብለው ከአለም እንደቀደሙ፣ እንዴት ብለው የአፍሪካ የነጻነትና ቀና የማለት ብስራት እንደሆኑ፣ እንዴት ብለው በሉአላዊነትና በክብር፣ በጀግንነትና በወንድማማችነት እንደቆሙ ነግረውናል። የአባቶቻችን እውነት ወደ ፊት ለመሄድ የወርቅ ምንጣፋችን ነው።

ያን ምንጣፍ የናቅን ጊዜ፣ ያን ምንጣፍ የተጸየፍን ጊዜ በደም የቆመውን ኢትዮጵያዊነት እየሻርን ነው። ያን ምንጣፍ “አይረባም” ያልን ቀን፣ ያን መረማመጃ “አሮጌ ነው” ያልን ቀን ማንነታችንን እየካድን ነው። በደም የተገመደ፣ በታሪክ፣ በባህል የተሳሰረ አንድነታችንን እያላላን ነው። ዓለም የሌላትን፣ በምንም የማናገኘውን ወርቃማ እድላችንን እያጣን ነው።

አባቶቻችን ወንድሙን ታግሎ የጣለ ጀግና አይባልም ሲሉን የወንድም ደም የራስ ደም ነው እያሉን ነው። ወንድምህ ቢያስቀይምህ በፍቅርና በይቅርታ እቀፈው፣ ይቅር በለው እያሉን ነው። ወንድሙን ታግሎ የጣለ ጀግና አይባልም ሲሉን አገር ማለት አንተና እሱ ናችሁ። ከአንተ ውስጥ እሱን አጉድለህ ሙሉ መሆን አትችልም። አንተ ኢትዮጵያዊ የተባልከው በእሱ ውስጥ ነው። እሱም ኢትዮጵያዊ የሆነው በአንተ በኩል ነው፤ እናም ቢገልህና ብትገድለው ኢትዮጵያን እየገደላችኋት ነው እያሉን ነው።

ሌላው ለሁላችንም አዲስ ያልሆነ ግን ደግሞ እምብዛም ስንጠቀምበት የማይስተዋል ስነቃል አለ። “ድር ቢያብር አንበሳን ያስር” የሚል። በዚህ የተጠቀሙ፣ ተጠቅመውም ያተረፉ ብዙ ኢትዮጵያውያን አሉ። አድዋን እና ሌሎች የጋራ ድሎቻችን በዚህ ስነቃል በኩል የተፈጠሩ ናቸው ማለት ይቻላል።

ሁሉንም ትተን እንኳን “ኢትዮጵያ” የሚለው ስም የተሳለውና የተቀለመው በዚህ ስነቃል በኩል ነው። ኢትዮጵያዊነት አንድ ትርጉም ቢኖረው አንድነት ነው የሚሆነው። ይሄ አንድነት ደግሞ በ“ድር ቢያብር አንበሳን ያስር” ምሳሌያዊ አነጋገር አማካኝነት እውቅና ያገኘ ነው። ታዲያ የእኛ መነጣጠል፣ የእኛ መለያየት ከየት የመጣ ነው?

በወንድም ደም ጀግና ከመሆን ይልቅ፣ በማይጠቅመንና አባቶቻችን ባላወረሱን እኔነትና ብቻነት ተነጣጥለን ከምንጓዝ መለያችን በሆነው የጋራ ስማችን አብረን ብንቆም ነው የሚያዋጣን። ዛሬ ላሉብን እና ነገ ለሚኖሩብን ችግሮቻችን ጀግና በሌለው በወንድም ሞት ከምንለፋ ተባድነንና ተረዳድተን እንደ አንበሳ ሊሰለቅጠን የደረሰ ችግራችንን ብንገጥመው ነው የሚሻለው።

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የሚለው አባባላችን በአሁኑ ዘመን ጥቅም ላይ ሲውል አይታይም። “ለምን?” ካልን መልሱ “በመለያየትና በመነጣጠል ስለሰለጠንን” ነው የሚሆነው። ስልጣኔአችንን ከአንድነት ካልጀመርንና በወንድማማችነት ካላበቃን ተጣልቶ መታረቅ፣ ተገዳድሎ መጨባበጥ ነው እጣ ፈንታችን የሚሆነው።

የሚያስፈልገን ተጣልቶ መታረቅ፣ ተገዳድሎ መጨባበጥ ሳይሆን ሳንጣላና ሳንገዳደል በፊት ችግሮቻችንን መፍታት ነው። ትላንትን መለስ ብለን ብናይ ደስታን የሚሰጠን ምንም ነገር የለም። ሞተንና ገለን የታረቅን ነን። ሳንሞትና ሳንገል ጀግንነታችንን በእርቅና በሰላም ውስጥ መፈለግ ነው እንደ አገር በረከት፣ እንደ ግለሰብ ጀግና የሚያስብለን።

በጦርነት ውስጥ ጀግና መሆን ይብቃን። ጀግና ለመሆን ከተሰናዳን ጀግና ልንሆንባቸው የምንችልባቸው እልፍ የድህነትና የኋላ ቀርነት ነውሮች አሉብን። ከእንግዲህ ባለችው ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ፖለቲከኛ፣ እንደ ዜጋና እንደ አንድ አገር ወዳድ ትውልድ ጀግንነታችን በፍቅርና በሰላም፣ በልማትና በይቅርታ ውስጥ እናድርገው።

ያለን አማራጭ ድር ቢያብር አንበሳን ያስር በሚለው ብሂል ላይ ቆመን እንደ አንበሳ እያገሳ ሊውጠንና ተስፋ ሊያስቆርጠን ፊታችን የቆመውን ድህነትና ኋላ ቀርነት መፋለም ነው። ስልጣኔን አንድ ቃል ቢገልጸው ጠንካራ ሀሳብ ከጠንካራ አብሮነት ጋር የሚል ይሆናል። ታሪኮቻችን ጦርነት የተቆራኛቸው ጠንካራ ሀሳብ ከጠንካራ ወንድማማችነት ጋር ስላጣን ነው።

ለዓለም ሰላም አስተዋጽኦ የነበራት አገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሰላም ያለህ በሚሉ የሰቆቃ ድምጾች መዋጧ አንድም ራስ ወዳድነት፤ አንድም ሰላምን በኃይል የማምጣት ልምምዳችን የፈጠረው ነው። በሀሳባችን ውስጥ ያለችውን ኢትዮጵያ ለመውለድ፣ ሁሌ ድምጽ ማጉያ በያዝን ቁጥር እንድትፈጠር የምንሻትን ኢትዮጵያ ሆና ለማየት ከለመድነውና ከተለማመድነው፣ አሸናፊ ከሌለው ግፊያ እንላቀቅ።

አንደኛነት ከሌለው የወንድማማችነት ግፊያና ትንቅንቅ ወጥተን የጋራ ቤታችንን መስራት ነው ከዓለም እኩል የሚያራምደን። ድር ቢያብር አንበሳን ያስር ብለን ስንነሳ ነው ሀይል የምናበጀው። ፖለቲካችን ሀሳብ የለውም። ካለውም ሩቅ የማይወስድ ቅርብ አዳሪ ሀሳብ ነው። ሀሳብ የሌለው ፖለቲካ ደግሞ እየገደለ የሚሞት፣ እያደማ የሚጨባበጥ ነው።

ጊዜው የሰላምና የእርቅ እንደመሆኑ እንደ ህዝብ የሚያስብ ፖለቲካና ፖለቲከኛ የምንሻበት ጊዜ ላይ ነን። እንደ ህዝብ ማሰብ ኢትዮጵያዊነትን ማስቀደም ነው። ከፖለቲከኞቻችን አፍ ይልቅ በህዝብ ልብ ውስጥ ያለችው ኢትዮጵያ ታስፈልገናለች። የፖለቲከኞቻችን ኢትዮጵያ የማስመሰል ኢትዮጵያ ናት። ይህን ሁሉ ዘመን ተጉዘን አልደረስንባትም። እናም በህዝብ ልብ ውስጥ ወዳለችው የአንድነትና የወንድማማችነት ኢትዮጵያ እንመልከት።

ነገ ከትላትና ከዛሬ የተሻለ እንደሚሆን ከሰላም ጅምሩ መረዳት ይቻላል። ሕወሓት ከፌደራል መንግስት ጋር እጅ ለእጅ በመጨባበጡ ምክንያት የምንናፍቀውን የሰላም አየር በመሳብ ላይ እንገኛለን። በሌላ በኩል የሸኔ ቡድን በድርድር ሰላም አውርዶ ሌላ መጨባበጥን ስናስተናግድ ያኔ ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል። እኔም ያንን እውነት ነው በህዝብ ልብ ውስጥ ያለችው ኢትዮጵያ ያልኳችሁ።

> **ከፖለቲከኞቻችን አፍ ይልቅ በህዝብ ልብ ውስጥ ያለችው ኢትዮጵያ ታስፈልገናለች። የፖለቲከኞቻችን ኢትዮጵያ የማስመሰል ኢትዮጵያ ናት። ይህን ሁሉ ዘመን ተጉዘን አልደረስንባትም። እናም በህዝብ ልብ ውስጥ ወዳለችው የአንድነትና የወንድማማችነት ኢትዮጵያ እንመልከት።**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ግብር ከፋዩንም ግብር ሰብሳቢውንም የታደገ በቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራር

**ወርቅነሽ ደምሰው**

አቶ ማስረሹ ፍቃድ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ግብር ከፋይ ናቸው። ሌላም ጊዜ እንደሚያደርጉት ሁሉ የግብር መክፈያ ወቅትን ጠብቀው ግብራቸውን ለመክፈል ወደ ቢሮው የሄዱበትን ቀን ያስታውሳሉ። ያን ዕለት የክፍያ አገልግሎቱ የሚሰጥበትን አሰራር ግን ወትሮ እንደሚያከናውኑት ሆኖ ሊያገኙት አልቻሉም፤ በዲጂታል ተቀይሯል።

አገልግሎቱን ለማግኘት የሚያስችላቸውን ቅጽ (ፎርም) እንዲሞሉ ተደረገ፤ ከዚያም በአጭር የጽሁፍ መልዕክት ማሳወቂያ ዘዴ በአጭር ጊዜ ውስጥ መረጃው ደረሳቸው፤ ምንም አይነት ምልልስ ሳያስፈልግ አስፈላጊው መረጃ በቅጽበጽ ተሞልቶ የተጠናቀቀና ክፍያውን በቴሌ ብር መፈጸም ቻሉ። በቴሌ ብር የክፍያ ሥርአት ግብራቸውን መክፈል መጀመራቸው የጊዜ ብክነትና ድካምን ማስቀረት እንደተቻለ ነው ማስረሹ የተናገሩት።

ቀደም ሲል የግብር ክፍያ ሥርአቱ ረጃጅም ሰልፎችን ጠብቆ የሚከናወን ከመሆኑ በተጨማሪ የክፍያ ሂደቱም ረጅም በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ አጠናቅቆ ለመጨረስ አስቸጋሪና የቀናት ጊዜን የሚወስድ ነበር ያሉት አቶ ማስረሹ፤ በአጠቃላይ አሰራሩ እጅግ ኋላ ቀርና ግብር ከፋዩን የሚያሰለች እንደነበር ያስታውሳሉ።

አዲሱ በቴክኖሎጂ የታገዘ የአሰራር ሥርአት ይሄን ሁሉ ችግር ማስቀረቱንም አመልክተዋል። ጊዜ ሳይወስድ በደቂቃዎች ውስጥ አገልግሎት አግኝቶ ክፍያ መፈፀም እጅግ እንደሚያስደስት ይገልጻሉ። ይህን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ቴክኖሎጂ ማስቀጠል እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፣ በተለይ ለቴክኖሎጂው መቆራረጥ እንቅፋት የሆኑትን ተከታትሎ ማስወገድ እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ።

አንዳንዴ ‹‹ሲስተም የለም›› የሚሉ ምክንያቶች አሁንም እንደሚሰጡና ይህም ተገቢ እንዳልሆነ ጠቁመዋል። ጊዜው ዘመናዊነትን እንደሚጠይቅ ጠቅሰው፣ ይህን አሰራር አጠናክሮ መቀጠል እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩት ወይዘሮ ሙና አሳየ በበኩላቸው ግብራቸውን ቢሮው በዘረጋው ዲጅታል ሲስተም ተጠቅመው በቴሌ ብር መክፈል መጀመራቸውን ይናገራሉ። ግብር ለመክፈል የግብር መክፈያ ማዕከላት ድረስ መሄድ አላስፈለጋቸውም፤ ባሉበት ሆነው ሞባይል ስልካቸውን ተጠቅመው በዲጅታል ሲስተም መክፈል እንደሚችሉ ካወቁ ጊዜ ጀምሮ ግብር ለመክፈል የሚያስፈልጓቸውን መስፈርቶች ካሟሉ በኋላ ግብር እንደሚከፍሉ ይገልጻሉ። ዲጂታል ዘዴን ተጠቅሞ ግብር ከመክፈል ባሻገር አሰራሩ የንግድ ፈቃዳቸውን በቀላሉ ለማደስ እንደረዳቸውም ጠቁመዋል።

ወይዘሮ ሙና በቀድሞው አሰራር ግብር ለመክፈል ከፍተኛ ጭንቀትና ውጣ ውረድ ይገጥም እንደነበር አስታወሰው ፤ እንግልቱና መጉላላቱ አሰልቺ ከመሆኑ የተነሳ የሚወሰደው ጊዜም ረጅም እንደነበረ ይገልጻሉ።“ አዲሱ አሰራር ይህንን ሁሉ ችግር እንደቀረፈ ጠቅሰው፣ ጊዜንና ወጪን በመቆጠብ በቀላሉ ግብር ለመክፍል ይረዳል” ይላሉ።

ዲጅታል ዘዴን ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል የሚሉት ወይዘሮ ሙና፤ እሳቸው የሚያውቋቸው የንግድ አጋራቸው በዲጂታል ሲስተሙ ተጠቅመው ለመክፈል ሲሞክሩ ሲስተሙ እንዳልተቀበላቸውም ጠቁመዋል። እነዚህ በዲጅታል አጠቃቀሙ ላይ የታዩ ችግሮችም ተፈትተው ዘመናዊ በሆነ መልኩ ቢሰራ የተሻለና የተቀላጠፈ አገልግሎት ማግኘት እንደሚቻል ነው ያስታወቁት።

የዘመናዊ አገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ የቢሮው የመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ አብዱላዚዝ ካሊፋ እንደሚሉት፤ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ከ449ሺ በላይ ግብር ከፋዮችን የሚያስተዳድር ግብር ሰብሳቢ ተቋም ነው። የከተማ አስተዳደሩ ሙሉ ለሙሉ የሚያስተዳድራቸው ከ320ሺ በላይ የሚሆኑ የደረጃ “ሐ”ግብር ከፋዮች ናቸው። የእነዚህ ግብር ከፋዮች ቁጥር በጣም ከፍተኛ ነው። የተገልጋዩ መብዛት አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ከፍተኛ ክፍተት እንዲኖር አድርጎል።

ቀደም ሲል ተቋሙ ግብር ለማስተዳደር የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀም ነበር። ግብር ከፋዩ ብዛት ያለው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ግን አገልግሎት አሰጣጡ ላይ የነበሩ በርካታ ተግዳሮቶች ተገልጋዩን ለእንግልት ሲዳርጉ ቆይተዋል። በመሆኑም ይህንን አሠራር ለመቀየር የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የአሰራር ለውጦች ለማምጣት ስትራቴጂ በመንደፍ ወደ ሥራ ተገብቷል።

በዚህም የግብር ከፋዩን ምልልስ ሊቀንሱ የሚችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ሥራ ላይ መዋል መቻላቸውን ነው አቶ አብዱላዚዝ ያብራሩት። እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በየታክስ ማዕከላቱ ተበታትኖ የነበረውን አሠራር በአንድ ላይ በማስተሳሰር ግብር ከፋዩን በተሻለ መልኩ ማስተናገድ የሚቻልበት የአሠራር ዘዴ ሥራ ላይ ውሏል። ለግብር ከፋዩ አማራጭ የክፍያ ዘዴዎች በመፍጠር፣ ክፍያ ማሳወቂያና ክሊራንስ የሚወሰድበትን ዘዴ ማመቻቸት ተችሏል። በአዲሱ አሠራር ከ320ሺ በላይ የሆኑ ግብር ከፋዮችን በማስተናገድ ግብር ለመወሰን፣ ክፍያ ለማስከፈል እና ክሊራንስ ለመስጠት የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ግብር ከፋይ በግብር ማሳወቂያ ወቅት አገልግሎቶች ለማግኘት ወደ አምስት ጊዜያት ወደ ገቢዎች ቢሮ መመላለስ ይጠበቅበት ነበር። ግብሩን ለማወቅ፣ ግብሩን ለማስወሰን፣ ውሳኔ ይሰጠኝ ለማለት፣ በውሳኔው መሠረት ክፍያ ለመፈጸም እና ለከፈለበት ማረጋገጫ (ክሊራንስ) ለመውሰድ ወደ ተቋሙ መመላለስ ይጠበቅበታል። ይህንን ሁሉ ካጠናቀቀ በኋላ ደግሞ ንግድ ፈቃዱን ለማደስ ወደ ንግድ ቢሮ መሄድ የግድ ይለውም ነበር።:

አሁን የተዘረጋው የአሠራር ሥርዓት ግን እነዚህን ሁሉ ምልልሶች እና እንግልቶች ቀንሷል የሚሉት አቶ አብዱላዚዝ፤ አዲሱ የአሠራር ዘዴ (ሲስተም) ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመሆን የኢታስ (የኦንላየን ታክስ አውቶሜሽን)ንና የቴሌብር ሲስተምን በአንድ ላይ በማስተሳሰር ለግብር ከፋዩ በአጭር የስልክ መልዕክት እንዲደርሰው የማድረግ ሥራ መሥራቱን ጠቁመዋል። ግብር ከፋዩ ወደ ተቋሙ መምጣት ሳያስፈልገው በ7075 አጭር የስልክ መልዕክት ግብሩን ካለበት ሆኖ መክፈል ይችላል ሲሉ አብራርተዋል።

በአዲሱ አሠራር ግብር ከፋዩ የትኛውም ቦታ ላይ ሆኖ የሞባይል ስልኩን በመጠቀም ግብሩን መክፈል ይችላል ያሉት አቶ አብዱላዚዝ፤ በሌላ በኩል ግብር ከፋዩ ከገቢዎች ቢሮ የሚላክለትን ቁጥር በመያዝ በየትኛውም የንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በኩል ቀጥታ መክፈል የሚችልበት አማራጭም እንደተመቻቸ ጠቁመዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በአጭር የስልክ መልዕክት አማካይነት የግብር ውሳኔው ለግብር ከፋዩ የሚላክ ሲሆን፤ ክፍያውን ደግሞ በቴሌ ብርና በንግድ ባንክ አማራጮች አማካይነት መክፈል የሚችልበት የአሠራር ዘዴ ተዘርግቷል። በመጨረሻ ለግብር ከፋዩ ማረጋገጫ ደረሰኝ (ክሊራንስ) እንዲደርሰው ይደረጋል። ይህ ደግሞ ንግድ ፍቃዱን በቀጥታ ለማሳደስ ያስችለዋል።

በአዲሱ አሠራር መሠረት የግብር ከፋዩ ውሳኔ በ7075 አጭር የስልክ መልዕክት አማካይነት ወደ ተመዘገበው የስልክ ቁጥር ይልካል። ግብር ከፋዩም በቴሌ ብር *127# በመደወል ከሚመጡት አማራጮች ውስጥ ግብር የሚለውን በመምረጥ ከገቢዎች ቢሮ በአጭር የስልክ መልዕክት የተላከውን ቁጥር ካስገባ በኋላ የሚመጡለት መረጃዎች የራሱ መሆናቸውን አረጋግጦ ይሁንታውን አሳይቶ ግብሩን መክፈል ይችላል።

ይህ የአሠራር ዘዴ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ የዋለው ከሐምሌ ወር 2014 ዓ.ም ጀምሮ ነው የሚሉት አቶ አብዱላዚዝ፤ ወደ ተቋሙ በመምጣት መስተናገድ ከሚጠበቅባቸው ግብር ከፋዮች መካከል ከ110ሺ በላይ የሚሆኑት በአዲሱ የአሠራር ዘዴ (ሲስተም) መስተናገዳቸውን አስታውቀዋል። የተቀሩት ግብር ከፋዮች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አሠራሩ እንዳልገቡም ገልጸዋል።

ቴክኖሎጂው ተቋሙ ባለው የሰው ኃይል ደንበኞቹን ለማስተናገድ ይቸገርበት የነበረውን ማስቀረቱን የገለጹት አቶ አብዱላዚዝ፤ አሠራሩን አጠናክሮ ለማስቀጠል



አቶ አብዱላዚዝ ከሊፋ

> **የመረጃ ለውጥ ያደረጉ ግብር ከፋዮች ቢሮ መምጣት እንደሚጠበቅባቸው አስታውቀዋል። እነዚህ ግብር ከፋዮች ወደ ቢሮ በመምጣት መረጃውን ወቅታዊ ማድረግ ወይም የተላከው መረጃ ትክክለኛ ካልሆነ ተቋሙ ዘንድ በመቅረብ እንዲያስተካክሉ የሚጠበቅባቸው መሆናቸውን ገልጸዋል**

ተደራሽ ባልሆኑ ቦታዎች ላይ መረጃና ስልጠና በመስጠት ሁሉም ግብር ከፋይ በዚህ ዘዴ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል ይላሉ።

ግብር ከፋይ በሙሉ ወደ አዲሱ አሠራር ያልገባበት ዋንኛ ምክንያት አንዳንዱ ግብር ከፋይ አዲሱን ሲስተም ስላልለመደው ከነባሩ አሠራር ቶሎ ያለመልቀቅ የሚታይበት በመሆኑ ነው አቶ አብዱላዚዝ የገለጹት። የአሠራር ሥርዓቱን በደንብ እስከሚለምድ ድረስ ወደ አዲሱ ሲስተም ስርዓት ለማስገባት በእጅጉ እንደሚቸገር ጠቁመው፤ ለዚህም ተከታታይ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እንደሚሰራ አመላክተዋል።

‹‹ይህ አሠራር በግብር አሰባሰቡ ሂደት ከፍተኛ ውጤት የተገኘበት ነው›› ሲሉም አቶ አብዱላዚዝ ይገልገጻሉ፤ ተቋሙ የሚሰራው በውስን የሰው ኃይል መሆኑንም ጠቅሰው፣ በግብር አሰባሰብ ላይ ከፍተኛ ለውጥ መምጣቱን ተናግረዋል። በተጨማሪም ተቋሙ ሠራተኞች በየዕለቱ ግብር ከፋዩን በማስተናገድ ሥራ ላይ ብቻ ከሚጠመድ ሌላ ትልልቅ ሥራዎች ለመሥራት ያስችላል። የተቋሙን ችግሮች ነቅሶ በማውጣት መፍትሔ ለማስቀመጥ የሚያስችል እድል የሚፈጥር ነው ይላሉ።

በሌላ በኩልም ለግብር ከፋዩ ጊዜውን፣ ገንዘቡንና ጉልበቱን እንደቆጠበለትም ነው የገለጹት። ግብር ከፋዩ ግብር ለመክፈል ያባክን የነበረውን ጊዜው ተቆጥቦ በንግድ ሥራ ላይ ትኩረት እንዲያደርግ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩንም ጠቅሰው፣ ግብር ከፋዩ አገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚያነሳውን ቅሬታ መፍታቱ በራሱ ትልቅ ውጤት መሆኑን ነው አቶ አብዱላዚዝ የሚገልጹት።

አሁን በተዘረጋው አሠራር ግብር ከፋዩ ወደ ተቋም መምጣት እንደማያስፈልገው ጠቅሰው፣ የመረጃ ለውጥ ያደረጉ ግብር ከፋዮች ቢሮ መምጣት እንደሚጠበቅባቸው አስታውቀዋል። እነዚህ ግብር ከፋዮች ወደ ቢሮ በመምጣት መረጃውን ወቅታዊ ማድረግ ወይም የተላከው መረጃ ትክክለኛ ካልሆነ ተቋሙ ዘንድ በመቅረብ እንዲያስተካክሉ የሚጠበቅባቸው መሆናቸውን ገልጸዋል።

አሠራሩ የሚሰራው በገባለት መረጃ መሠረት ነው የሚሉት አቶ አብዱላዚዝ፤ በተለይ በውክልና በሚሰሩ ንግዶች ላይ የገባው መረጃና ያለው እውነታ ሊለያዩ እንደሚችሉም ጠቅሰው፣ ለአብነት መረጃውን ያስገባው ሰው እና አጭር የስልክ መልዕክቱ የሚደርሰው ሰው የተለያየ ሊሆን እንደሚችል ይናገራሉ። በዚህ ጊዜ የመረጃ ጥራት ችግር በመኖሩ ውሳኔው እንደገና የሚወሰንበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል አመላክተዋል።

በሌላ በኩል በተቋሙ የስልክ መረጃ በሚሞላበት ጊዜ የቁጥር ስህተት ሊፈጸም እንደሚችል ጠቅሰው፣ በዚህ ጊዜ መልዕክቱ ለተሳሳተው ሰው ሊደርስ የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጠር እንደሚችል አልሸሸጉም። በተመሳሳይ ግብር ከፋዩ ደግሞ ስልኩን ቁጥሩን ሲያስመዘግብ በትክክል የማያስመዘግብ ሁኔታ በመኖሩ ያብራራሉ።

አቶ አብዱላዚዝ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች መሠረት የመረጃ ጥራት ችግር ሊያጋጥም ይችላል ባይ ናቸው። “በዚህ አሠራር ሥርዓት መሠረታዊ ችግር የሆነው አንዱ የመረጃ (የዳታ) ጥራት ችግር ነው” ያሉት አቶ አብዱላዚዝ፤ አሁን በተገኘው ልምድና ተሞክሮ የተሻሉ የአሠራር ዘዴዎችን ሥራ ላይ ለማዋል እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ሙሉ ለሙሉ የሚያስተዳደራቸው የደረጃ ‹‹ሐ›› ግብር ከፋዮችን እንደሆነ የሚገልጹት አቶ አብዱላዚዝ፤ ሌሎች ግብር ከፋዮች የሚስተናገድበት የአሠራር ሥርዓት የተለየ መሆኑንና ከፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር ጋር በጋራ የሚሰሩ ሥራዎች እንዳሉም ይናገራሉ።

በቀጣይም ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚሰጡ አገልግሎቶች ፈጣንና ቀልጣፋ የሚያደርጉ አሠራሮችን የመዘርጋቱ ተግባር ተጠናክሮ እንደሚያስቀጥል የሚገልጹት አቶ አብዱላዚዝ፤ ዘመኑን የሚመጥን ቴክኖሎጂ በመጠቀም አገልግሎቶችን በየጊዜው ለማዘመን ትኩረት ተደርጎ ይሰራል ይላሉ። ግብር ከፋዩ ማህበረሰብም ይህንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተቋሙ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ እምነት ማሳደር እንዳለበት አስገንዝበዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# በቴክኖሎጂ የተደገፈ የነዳጅ ግብይት ፋይዳ

ክብረአብ በላቸው

በኢትዮጵያ ለነዳጅ በሚደረገው ድጎማ ምክንያት ከዓለም አቀፍ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በአነስተኛ ዋጋ መሸጡ ለኮንትሮባንድ ንግድ ተጋላጭ አድርጎታል። ወደ ውጭ አገራት በመውጣቱ በነዳጅ ግብይት ላይ ያለውን ክፍተት ለመቅረፍ የነዳጅ ግብይት በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ስርዓት እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል። ይህንን ተከትሎ የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከግንቦት ወር ጀምሮ በመላ አገሪቱ የነዳጅ ግብይት በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ስርዓት ተፈፃሚ እንደሚሆን አስታውቋል።

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፤ ምንም እንኳ ጊዜው አጭር ቢሆንም የነዳጅ ግብይት ሪፎርም ከተደረገ ወዲህ መሻሻሎች መኖራቸውም አመልክቷል። የነዳጅ ግብይት ባለፉት ሃያ ዓመታት የዋጋ አሰራሩ ክፍተት የነበረበት በመሆኑ፤ ለነዳጅ ዋጋ ማረጋጊያ የሚሰጠው ፈንድ አገሪቱን ለእዳ እየዳረጋት ቆይቷል። በዚህም የነዳጅ ግብይቱን ስርዓት ለማስያዝ የኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ስርዓት ተዘርግቶ ፍትሃዊ የነዳጅ ስርጭትና አጠቃቀም እውን እንዲሆን የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተጠቁሟል።

በሌላ በኩል በሙከራ ደረጃ እየተተገበረ የቆየው ይህ የአሰራር ስርዓት ከሚያዚያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ የነዳጅ ማደያዎች ግብይቱ ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ መንገዶች ብቻ እንደሚፈጸም ያስታወቀው ደግሞ የነዳጅና ኢነርጂ ቁጥጥር ባለስልጣን ነው። ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በአዲስ አበባ የኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ስርዓቱ በአማራጭነት በሙከራ ደረጃ እየተተገበረ መቆየቱን ገልጾ፤ ከሚያዚያ 16 2015 ዓ.ም ጀምሮ የነዳጅ ግብይቱ በአስገዳጅ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ መንገዶች ብቻ እንደሚፈጸም አሳውቋል። በመሆኑም ህብረተሰቡ ማንኛውም የነዳጅ ግብይት በኤሌክትሮኒክስ ብቻ የሚፈጸም መሆኑን ተገንዝቦ ከወዲሁ አስፈላጊውን ዝግጅት ሊያደርግ እንደሚገባ ማሳሰቢያ አስተላልፏል።

ኢትዮ ቴሌኮም በበኩሉ የነዳጅ ግብይትን በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ መንገዶች በማድረግ ረገድ በ “ቴሌ ብር” ውጤታማ ስራ ሲሰራ መቆየቱን ገልጿል። በሙከራ ትግበራ በቆየባቸው ባለፉት ዘጠኝ ወራት በ “ ቴሌ ብር “ ብቻ ከ30 ቢሊዮን ብር በላይ የነዳጅ ግብይት መፈጸሙን አመልክቶ። በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ 153ቱም የነዳጅ ማደያዎች የነዳጅ ግብይቱ በቴሌብር በተሳለጠ መልኩ እንዲከናወን እና ለደንበኞች በፍጥነት የተሳለጠ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ መሆኑን በተጨማሪም የነዳጅ ግብይቱን በአግባቡ በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ መንገዶች ለማከናወን የሚያስችል ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መገንባቱንም አስረድቷል።

አሰራሩ መንግስት የነዳጅ ምርት ከመነሻው እስከ መድረሻው በሚኖረው የስርጭት ሂደት መረጃ እንዲኖረው እና ነጋዴዎችም ግብርና ታክስ እንዳያጭበረብሩ በማድረግ ቴክኖሎጂው ትልቅ ሚና እንዳለው ደግሞ የተለያዩ ባለሙያዎች ይገልፃሉ። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን የሚሉት አላቸው። የኢኮኖሚ እና የምጣኔ ሃብት ባለሙያው አቶ ወሰንሰገድ አሰፋ እንደሚናገሩት፤ የእቃ ግብይት የክፍያ አሰራር ዘዴ ከኢኮኖሚ መስኮች አንዱ ነው። ግብይት ሄዶ ሄዶ እቃ መሸጥ በመሆኑ፤ ዋነኛው የታችኛው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚሳለጥበትን መንገድ በቀጥታ (በኦንላይን) ማድረግ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

አሁን በነዳጅ ላይ ብቻ የተፈፀመ ቢሆንም፤ ወደ ፊት ግብርና ላይ ገበሬውን ማዳረስ ቢቻል እንዲሁም ደግሞ ሌላ አገልግሎት የሚሰጡ አካላት አምራቾች እና ሸማቾች በአካል መገናኘት ሳይጠበቅባቸው የኦንላይን ግብይት መፈፀም መቻል እንደ አገር በብዙ መልኩ ከፍ ያለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው። ጥሬ ገንዘብ በኪስ ይዞ መዞርን ያስቀራል። ይሄ ደግሞ ፋይዳው ብዙ መሆኑን ያስረዳሉ።

**‹‹አዳዲስ ነገር ሲጀመር ለጊዜው ፍራቻ ይኖራል። በሂደት ግን አሰራሩን ሁሉም ሲለመድ በጣም ቀላል እንደሆነ ይታወቃል። ወደ ፊት ውጤታማ እንደሚሆን አያጠያይቅም››**

እያንዳንዱ ብር ሲያረጅ እንደ አዲስ በብሔራዊ ባንክ መታተም ይኖርበታል። ብር ለማሳተም ተጨማሪ ወጪ ይወጣል። በተለይ በነዳጅ ግብይት አካባቢ ላይ የብር ዝውውሩ በጣም ከፍተኛ በሆነበት ሁኔታ የብሮች መበላሸት እና ብሮች በተበላሹ ቁጥር ደግሞ መንግስት የተበላሹትን ብሮች ለመተካት የሚያወጣውን የውጭ ምንዛሬ በከፍተኛ ደረጃ ያስቀራል። ስለዚህ ከጥሬ ብር ንክኪ መውጣት ከተቻለ መልካም ስለመሆኑ ያብራራሉ። እንደ አቶ ወሰንሰገድ ገለፃ፤ የነዳጅ ማደያዎች ላይ በቢሊየኖች ገንዘብ ይዘዋወራል። ይህ ሁሉ እስከ አሁን የሚዘዋወረው በካሽ ነበር። በካሽ አለመሆኑ የመበላሸት ፍጥነቱን ይቀንሳል። ይህ ደግሞ የውጪ ምንዛሬ ወጪን ይቀንሳል።

በሁለተኛ ደረጃ በገቢዎች የግብር አከፋፈል በኩል በማየት አቶ ወሰንሰገድ ለአብነት ሲያነሱ ለድርጅቶች የነዳጅ ወጪ ይወራረዳል። ከዚህ አኳያ ከተመለከትነው ጥሬ ደረሰኝ ሳያስፈልግ በቴሌ ብር ወይም በሌላ የክፍያ አማራጭ አንድ ግለሰብ በትክክል ለነዳጅ ያወጣውን ወጪ በቀላሉ ድርጅቱም ሆነ መንግስት ማወቅ ይችላሉ። ስለዚህ ከታክስ ጋር ተያይዞ ያሉ ነገሮችን በቀላሉ መፍታት ይቻላል። ሌላኛው ደግሞ እያንዳንዱ ሰው በግል ለነዳጅ የሚያወጣውን ፍጆታ መጠን ያውቃል። የሁለት ሺህ ብር እና የሶስት ሺህ ብር ነዳጅ ሲሞላ ምን ያህል ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚቻል በማረጋገጥ፤ በቀላሉ የግል የነዳጅ ፍጆታን ማወቅ ቀላል ይሆናል ይላሉ።

የግብይት ሂደቱን በጣም ስለሚያቀላጥፈው በትክክል ከነዳጅ ሽያጭ የሚሰበሰበውን ገቢ ማወቅ እንዲቻል ያደርገል፤ ነዳጅ የሚያከፋፍሉ ድርጅቶችም ዕለታዊ ገቢያቸው ስንት እንደሆነ ቁጭ ብለው በአካል ብር ቆጥረው መረከብ ሳይኖርባቸው ባሉበት ቦታ ድርጅታቸው ስንት እንደሸጣ፤ ስንት ሊትር ነዳጅ እንደቀረው፤ በሞባይላቸው መከታተል እንዲችሉ ያደርጋቸዋል ብለዋል።

ቴክኖሎጂ በመጣ ቁጥር የቴክኖሎጂ ዕድገት ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት አለው የሚሉት አቶ ወሰንሰገድ፤ ቴክኖሎጂ ባደገ ቁጥር ታክስ ማጭበርበር አይቻልም። ገንዘብ ይቆጥባል፤ ጊዜ ይቆጥባል፤ በተጨማሪ ለትራንስፖርት ይወጣ የነበረውን ወጪ መቆጠብ ያስችላል። እነኝህ ሁሉ ነገሮች ሰይባከኑ መቅረታቸው የኢኮኖሚ እድገቱ ላይ ቀጥተኛ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ብለዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የአሰራር ለውጥ ሲመጣ በለውጡ የሚጠቀም አካል ይኖራል። የሚጎዳ አካል ሊኖርም ይችላል የሚሉት የኢኮኖሚ ባለሙያው፤ አንዳንድ ጊዜ ነዳጅ ለቀዱ አካላት ተጨማሪ ጉርሻ መስጠት ወይም ደግሞ በማጭበርበር ዋጋ ከፍ እና ዝቅ ማድረግ መኖሩ ሲነገር ነበር። አሁን ግን ቀጥታ ወደ ባንክ ሒሳብ ስለሚገባ እጃቸው ላይ ምንም አይነት የጥሬ ገንዘብ ዝውውር አይኖርም። ተንጠባጥቦ የሚቀር ገንዘብ የመገኘት እድላቸው በጣም ያንሳል፤ በዚህ ምቾት የማይሰማቸው አካላት ሊኖሩ ይችላሉ፤ ይሄ ደግሞ የሚጠበቅ እና ተፈጥሯዊ እንደሆነ ነው የተነገሩት።

የቴክኖሎጂ ባለሙያው አቶ አበበ በቀለ በበኩላቸው፤ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ አይሆንም። አንድ ነገር ሲመጣ ጥቅም እንዳለው ሁሉ ጉዳትም ሊኖረው ይችላል፤ የሞባይል ገንዘብ ዋና አላማው የግብይት ሂደቱን ጥሬ ገንዘብ አልባ ማድረግ ነው። ሰው ገንዘብ በእጁ መያዝ ሳይጠበቅበት የሚፈልገውን ግብይት ይፈፅመል። ይህ የግለሰብን ደህንነትንም ያስጠብቃል፤ የግዴታ ምርጥ ስልክ ሳያስፈልግ በማንኛውም ስልክ አገልግሎት ማግኘት የሚቻል በመሆኑ ብዙ የሚያስጨንቅ አይደለም ይላሉ።

እንደ ኢኮኖሚስቶች አቶ ወሰንሰገድ ሁሉ፤ አቶ አበበም በቴክኖሎጂው መጠቀም ከተቻለ አንድ ነዳጅ ማደያ በቀን ውስጥ ያከናወነውን የግብይት መጠን ማወቅ ይቻላል። የመጣው ነዳጅ በትክክል ተጠቃሚ ጋር ደርሷል የሚለውን ሁሉ በመረዳት፤ ከብልሹ አሰራር የፀዳ አገልግሎት እንዲኖር ያደርጋል። ወደ ፊት ይሄንን አሰራር ከአቅጣጫ ጠቋሚ ቴክሎጂ ጋር፣ ከኪሎ ሜትር ጋር ማገናኘት ከተቻለ ደግሞ የበለጠ ተጠቃሚ ሊያደርግ ይችላል ይላሉ። የተጀመረው አሰራር እጅግ በጣም ጠቃሚ እና ውጤታማ እንደሚሆን ጥርጥር እንደሌላቸውም ነው የተናገሩት።

አዳዲስ ነገር ሲጀመር ለጊዜው ፍራቻ ይኖራል። በሂደት ግን አሰራሩን ሁሉም ሲለመድ በጣም ቀላል እንደሆነ ይታወቃል። ወደ ፊት ውጤታማ እንደሚሆን አያጠያይቅም ብለዋል። በዓለም ዙርያ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ይጠቀማሉ። ባደጉ አገራት ብቻ ሳይሆን፤ ጎረቤት አገራት ከኢትዮጵያ በተሻለ ሁኔታ ገንዘብን በሞባይል ያዘዋውራሉ። በከተማ ብቻ ሳይሆን ገጠር ውስጥ ሳይቀር፤ የግድ ባንክ ሄዶ ገንዘብ አውጥቶ አገልግሎት ወደሚገኝበት ቦታ መሄድ አይጠበቅም። ካሉበት በእጇ ስልካቸው ይጠቀማሉ። በኢትዮጵያም በተመሳሳይ መልኩ የትም ቦታ ሆኖ የሚፈልገውን አገልግሎት ማግኘት መቻል አለበት።

ዜጎች ከነዳጅ ባለፈ በሌሎች ግብይቶች ላይም ቢጠቀሙት መልካም ነው። ምክንያቱም ለአገር ያለው አስተዋፅኦው ትልቅ ነው። ጅምር ላይ ያለ አሰራር በመሆኑ የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ የሚሉት አቶ አበበ፤ የኢንተርኔት አቅርቦት ክፍያ፣ የኃይል አቅርቦት ክፍያ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ተቋማት ላይም በመተግበር አገራዊ ተቋማት በመተጋገዝ እና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በመወጣት ቴክኖሎጂው በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል መስራት አለባቸው። በዚህ መልኩ ከተሰራ ምንም የማይቀረፍ ችግር አይኖርም። ይሄ የሞባይል የክፍያ ስርዓት በአዲስ መልክ እንደመጣ ሁሉ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ፈጠራ የታከለበት መንገድ ተጠቅመን ከሰራን ውጤታማ እንሆናለን ብለዋል።

ቴክኖሎጂው በኢትዮጵያ ሲተገበር ገና አዲስ ከመሆኑ አንፃር ምን ምን ችግር ያጋጥማል? ማወቅ የሚቻለው የሚለውን በሂደት ነው፤ ከአሁኑ ሁሉንም ችግር ዘርዝሮ እንዲህ እና እንዲያ ነው ማለት አይቻልም። ጥቅም እና ጉዳት አለው። ግን የትኛው ይበልጣል ወይም ሚዛን ይደፋል የሚለው ትልቁ ነገር በመሆኑ ጠቃሜታው ከፍተኛ መሆኑን አምኖ እና ቴክሎጂውን ተቀብሎ ችግሮችን እየተቋቋሙ መስራት ተገቢ እንደሆነ ተናግረዋል።

በአጠቃለይ የቴክኖሎጂ እድገት በጨመረ ቁጥር የኢኮኖሚ እድገት በዛው መጠን ይጨምራል። ስለዚህ ይህንን የኦንላይን የግብይት ስርዓት ወደ ሁሉም የገበያ መስኮች ማስፋት መቻል አገራዊ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍተኛ እንደሆነ ባለሙያዎቹ ገልፀዋል።




ማህበራዊ

# ሴቶች

# ሴቶችን ከሱሰኛነት የመነጠል ንቅናቄ

ሰላማዊት ውቤ



የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ



የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሙና አህመድ



አቶ ኤሊያስ ካሳይ



ፕሮፌሰር ሰለሞን ተፈራ

እንደ አጠቃላይ ሲታይ፣ የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኞች በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ ይሳናቸዋል፤ ብቸኝነት ያስደስታቸዋል። እንዲሁም፣ ሰርክ የሚያስደስቷቸውና የሚወዷቸው ነገሮች አንዳንዴ የሚረብሿቸው፤ በተጨማሪም የሚያስፈሯቸው ጊዜ አለ። እነዚህ ችግሮች በማህበረሰቡ ውስጥ ድርብርብ ኃላፊነት ባለባቸው ሴቶች ላይ ሲከሰቱ ደግሞ ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ የሚያስከትሉበት ሁኔታ እንደሚፈጠር የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህን ታሳቢ በማድረግ ከሰሞኑ በስካይላይት ሆቴል፣ “ከሚያዝያ 2015 እስከ ሚያዝያ 2016 ዓ.ም” የሚዘልቅ የፀረ አደንዛዥ ዕፆች የንቅናቄ መድረክ ይፋ አድርጎ ነበር። ወጣት ሴቶችን፣ እንዲሁም አጠቃላይ ወጣቶችን ለመታደግ በተጀመረው በዚህ የንቅናቄ መድረክ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትሯ ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ በክብር እንግድነት ተገኝተው ነበር። በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታዋ ወይዘሮ ሙና አህመድም የተገኙ ሲሆን ሁለቱም በየፊናቸው ባስተላለፉት መልክት መጤ ባህሎችም ሆኑ አደገኛ ዕጾችና የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች በይበልጥ ሴቶችን የሚጎዱበት ሁኔታ መኖራቸውን አንስተዋል። ከሴቶች ጋር ተያይዞም ሴቶች በማህበረሰብ ውስጥ ካላቸው ከፍተኛ ኃላፊነት አንፃር በችግሩ መጠመዳቸው፤ ማህበረሰቡም ለቀውስ የሚዳረግበት ሁኔታም እንደሚፈጠር ተናግረዋል። ሴቶች በተፈጥሮ ባገኙት ልጅ በመውለድ ሕይወትን ከማስቀጠል ታላቅ ፀጋ ጋር ተያይዞ ሱሰኛና ጤናማ ያልሆነ ልጅ ከመውለድ ጀምሮ ቀውሱ የሚባባስበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችልም ያወሳሉ።

እንደ ኢትዮጵያ ከጠቅላላው የሕብረተሰብ ክፍል የሴቶች ቁጥር ከግማሽ በላይ እንደሆነ ያወሱት ሚኒስትር ኤርጎጌ ሚኒስቴር መሥርያ ቤታቸው የእነዚህ ሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ደፋ ቀና እያለ መገኘቱንም ጠቁመዋል። «ይህንን ከግብ ለማድረስ አሁን ላይ በአገራችን ከፊተኞቹ ዘመናት የተሻለ ምቹ ሁኔታ አለ» ይላሉም። ከፖለቲካዊ ምቹ ሁኔታዎች መካከልም የሴቶችን መብትና ጥቅሞች ማስከበርና ማረጋገጥ አስመልክቶ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውንና የፈረመቻቸው ሕጎች በዋነኛነት ይጠቀሳሉ ባይ ናቸው። በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ካሉት 20 የካቢኔ አባላት 50 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸውንም በማሳያነት ያነሳሉ። የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢዋን ጨምሮ ቁጥራቸው በርከትከት ያለ ሴቶች በየደረጃው መቀመጣቸውም ከዚሁ ምቹ ሁኔታ የሚደመር መሆኑን ያወሳሉ። እንዲህም ሆኖ በክልል፤ በዞንና በወረዳ ደረጃ የሴቶች ቁጥር ከላይ በመጣበት አግባብ የሚሄድበት ሁኔታ አለመኖሩ ሌላው ብዙ ትግልና ሥራ የሚጠይቅ ፈተና መሆኑንም ይጠቁማሉ።

እዚህ ላይ ሴቶች በአብዛኛውም ወጣት ሴቶች የወንዶቹን ያህል እንኳን ባይሆንም በትንሹም ቢሆን በመጤ ባህል፤ የአልኮል ይዘት ባላቸው መጠጦችና በአደገኛ እጾች ሱሰኝነት ተጠምደው መገኘታቸውን፤ በዚሁ ሰበብም ማህበረሰባዊ ቀውስ መፈጠሩ ፈተናውን በእጅጉ የሚያከብደው መሆኑንም ይጠቁማሉ። ችግሩ በራሳቸው፤ በጤናቸው፤ በትምህርታቸው፤ በውሳኔ ሰጪነታቸው፤ በኑሯቸው፤ በሚተኩት ልጅ (ትውልድ) ብሎም በሕብረተሰቡ፤ እንደ አጠቃላይም በአገር ላይ ስር የሰደደ ጉዳት ያደርሳል። ሴቶችን ለማብቃት፤ የውሳኔ ሰጪነት ሚናቸውን ለማሳደግና የፖለቲካ ተሳትፏቸውን በማጎልበት በሁሉም የልማት ዘርፎች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ፤ እንዲሁም፣ ለአገሪቱ ልማት እና እድገት መሰረት እንዲሆኑ ለማስቻል የግድ አስቀድሞ በሱሰኝነት ችግር እንዳይወድቁ መሥራት ያስፈልጋል። የገቡት እንዲወጡ መስራትም ለነገ የማይባልና በርብርብ የሚከናወን የዛሬ የቤት ሥራ መሆን ይኖርበታል። የንቅናቄ መድረኩን እንደ አገር ማስጀመር ያስፈለገውም አጠቃላይ ወጣቱን፤ በዚሁ ዕድሜ ክልል ያሉ ወጣት ሴቶችን እንዲሁም አጠቃላይ ተጋላጭና ሰለባ የሆኑ ሴቶችንና ሌሎች የማህበረሰቡ ክፍሎችን ለማዳንም እንደሆነ ሚኒስትሯ አስምረውበታል።

የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሙና አህመድም የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች፤ አደገኛ ዕጾችና መጤ ባህሎች አነሰም በዛ በሴቶች ላይ፣ በተለይም በሴት ወጣቶች ላይ የሚያደርሱት ተፅዕኖ ሰፊ ማህበራዊ ቀውስ የሚያስከትል በመሆኑ ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ ፈጣን መፍትሄ የሚሻ መሆኑን ነበር በመልክታቸው የተናገሩት። «ወጣት በማንኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ የአፍላ ጉልበት፤ የብሩህ አእምሮና የእምቅ ኃይል ባለቤት ነው» ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ ቀጣዩ ትውልድ የተሻለ ሆኖ መገኘት የሚችለው ይሄን ፀጋውን በአግባቡ ተግባር ላይ ሲያውለው ነውም ባይ ናቸው።

እንደ የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሙና ገለፃ ወጣቶች አልባሌ ቦታ እንዳይውሉ የስብዕና ግንባታ ወይም የመዝናኛ ማዕከላት መገንባትና ሴት ወጣቶችን ጨምሮ ሁሉም በሱስ የተጠመዱ ወጣቶች በፍትሀዊነት ከሱስ እንዲላቀቁ ማድረግ ያስፈልጋል። መፍትሄውም ይኸው ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ የተገነቡት 113 ስብዕና ማእከላት ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉ እንደሆነም በመድረኩ ላይ ተነግሯል። እንደ አገር ሲታይ ደግሞ ቁጥራቸው እጅግ ከፍተኛ ማዕከላት መኖራቸውንና ማዕከላቱ በትክክል ለወጣቱ፣ በተለይም ከመረጃ ለራቁት ሴቶች መረጃ በማቀበል፣ ስልጠና በመስጠትና የሚፈለጉትን ሥራዎች በመሥራት ረገድ ሁሉም የሚጠበቅባቸውን በእኩል ደረጃ ተወጥተዋል ማለት እንደማይቻልም ይጠቅሳሉ። ከ3ሺህ በላይ የስብዕና ግንባታ ማዕከላት ቢኖሩም ሥራ ላይ የዋሉት 1ሺ 545 ብቻ በመሆናቸው እነዚህን የማጠናከር ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ሚኒስትር ዴኤታዋ ያሳስባሉ።

ጾታ ሳይለይ ሁለቱም ወጣቶች አልባሌ ቦታ እንዳይውሉ ስብዕና ማዕከላት ሄደው የ“ዋይፋይ”፤ የቤተ መጽሐፍት፤ ስልጠናና ሌሎች አገልግሎቶች እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ እየተሰራ የተመጣበት ሁኔታ መኖሩንም የተናገሩ ሲሆን፤ አደንዛዥ ዕጾች፤ ከኛ ባህሎች ጋር የሚቃረኑ መጤ ባህሎችን በተመለከተ የሚያስከትሉትን ጉዳት የማስተማር ሥራም እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል። ሆኖም፣ በግምገማቸው እንዳረጋገጡት የተሰራው ስራ በቂ አለመሆኑን፤ ለዚህም ማሳያው ሱሰኝነት እየቀነሰ ሳይሆን እየጨመረ መምጣቱ መሆኑን ተናግረዋል። በመሆኑም፣ በቀጣይ ሕይወት አስቀጣይ ሱሰኛ ሴት ወጣቶችም ላይ ሆነ በአጠቃላይ ወጣቶች ላይ በቅንጅት ይሰራል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ከሆነ፣ ወጣት ሴት ስትሆን ደግሞ ሴቲቱ በማህበረሰብ ውስጥ ካላት ዘርፈ ብዙ ኃላፊነት አንፃር ጉዳቱ እጥፍ ድርብ ነው የሚሆነው። በመሆኑም ንቅናቄው በሁሉም አካላት ርብርብ ታግዞ ሊካሄድ ይገባል ሲሉም ወይዘሮ ሙና አህመድ ሕዝባዊ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

ወይዘሮ ባንቹ ሙሉጌታ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ማብቃት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አደንዛዥ ዕጾችና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶች ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ቀላል የሚባል እንዳልሆነ ይናገራሉ። ሴቶችን ለመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያጋልጡም ሁኔታዎች መኖራቸውንም ያነሳሉ። በዚሁ ዙርያ የተሰሩ ጥናቶችን መሰረት አድርገው እንዳብራሩት ወሲባዊ ፊልም፤ የምሽትና የቀን ጭፈራ ቤቶች፤ የጫት መቃሚያና ሲሻ ቤቶች፤ የመዝናኛ፣ የመገናኛና በይነ መረቦች ይጠቀሳሉ።

መሪ ሥራ አስፈፃሚዋ ዓለማቀፋዊነት የቤተሰብ ትስስር መላላት፤ የወንድ አቻ ግፊትና ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ሁኔታም ለችግሩ አጋላጭ ምክንያቶች እንደሆኑ ተናግረዋል። የወንዶች ብቻ ሳይሆን የአልኮል መጠጦችና የፀረ አደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚ ሴቶችና ሴት ወጣቶች ቁጥር እየተበራከተ በመምጣቱ አንድ ዓመት የዘለቀ የንቅናቄ መድረክ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። አብዛኛው የችግሩ ሰለባዎች ወንዶች መሆናቸው በጥናት መመላከቱን ወይዘሮ ባንቹ ያወሳሉ። ሆኖም ወንዶች ናቸው ሰለባዎቹ ሲባል ሴቶች ሰለባ አይደሉም ማለት እንዳልሆነ ይጠቅሳሉ። ሁሉንም ማህበረሰብ፤ በተለይም ሴቶችን የሚመለከት ክፍል በመኖሩ ሴቶች ከዚህ ችግር እንዲወጡ ይሰራል። በጥናቱ ላይ 4 ነጥብ 4 በመቶው በአጠቃላይ ካለው ወጣት አንፃር ሁሉም ሱሰኛ ነው ባይባልም ተጠቃሚ መሆኑን እንደሚያሳይ ይጠቅሳሉ። ከስብዕና ግንባታቸው ጋር ተያይዞ አደንዛዥ ዕፅን መጠቀም የጤና፤ የስነ ልቦናና የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ቀውሶችንም ያስከትላል። ከእነዚህ ቀውሶች ለመታደግ ስብዕና ግንባታ ላይ መሥራት ይገባል።

መሪ ሥራ አስፈፃሚ ባንቹ እንደሚሉት ሁሉም የችግሩን አሳሳቢነት እያየ ነው ያለው። ቁርጠኝነቱ የሚረጋገጠው እንደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በቀጣይ እንዴት ይፈፀማል ብሎ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን ሲሰራ ነውና ይህንን ይሰራል። ከዚህ በፊት ሥራዎች አልተሰሩም ሳይሆን ሚኒስቴሩ በየዓመቱም ሲሰራ ነው የቆየው፤ ክልሎችም እንዲሁ። አሁንም ሚኒስቴሩ አፈፃፀሙን ይከታተልና ይቆጣጠራል። ክፍተቶችም ካሉ የእርምት ሥራ ይሰራል። ተጨባጭ ለውጥ ማምጣትም ተችሏል። በችግር ውስጥ የነበሩና ከችግር በመውጣታቸው በንቅናቄው መድረክ ለመሳተፍ የቻሉ ማሳያ ናቸው። ሆኖም የመጣው ለውጥ አሁን ባለው ሁኔታ በሚፈለገው ልክ አይደለም።

ሌላው ጥናት አቅራቢ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ (ጥቁር አንበሳ) የአእምሮ ሕክምና ትምህርት ክፍል ባልደረባ የሆኑት ፕሮፌሰር ሰለሞን ተፈራ ናቸው። በግል የሬናሰንት የአእምሮ ሕክምናና ተሀድሶ ማዕከል መሥራችና ዋና ሥራ እስኪያጅ ናቸው። በችግሩም ላይ ለበርካታ ዓመታት በርካታ ስራዎችን ሰርተዋል።

ፕሮፌሰር ሰለሞን ከንቅናቄው ጋር በተያያዘ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡ ሲሆን፣ ከጥናታቸው ተነስተው እንደሚሉት መጤ ባህሎች፤ በፋብሪካና በቤት ውስጥ በጎጆ ኢንዱስትሪ በሚመረቱ የአልኮል መጠጦች፤ እንዲሁም፣ በአደገኛ ዕጾች ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ተጎጂዎች ናቸው። ይሄ በሳይንሱም የተረጋገጠ ዕውነታ ነው። ለምሳሌ የአልኮል ይዘት ያላቸውን መጠጦች አብዝተው የሚጠቀሙ ሴቶች በጽንስ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል መገንዘብ አለባቸው። እንደውም በአሁኑ ሰዓት ዓለም ዓቀፍ ጥናቶች ላይ ተመስርቶ የወጣው መመሪያ ነፍሰ ጡር ሴት የአልኮል ይዘት ያለባቸውን መጠጦች ፈጽሞ መጠቀም የለባትም። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የትኛውም የአልኮል ይዘት ያለው መጠጥ ጽንስን ስለሚጎዳ ነው። ነፍሰ ጡር ሆነው መጠጥ የሚጠጡ ሴቶች የእርግዝና ወቅት ከጠላና ጠጅ ጀምሮ በቤት ውስጥ የሚመረት ቢራም ሆነ ጠጅና አረቄ በየትኛው መጠን መጠቀም በጽንሱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያስከትል በጥናት በመረጋገጡ ተከልክሏል።

በርካታ ሴቶች በእርግዝና ወቅት፣ በተለይም የበዓላት ሰሞን የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች እንደሚጠጡ ይታወቃል የሚሉት ፕሮፌሰሩ ለነዚህ ነፍሰ ጡር ሴቶች ሲመክሩም፣ “በልጃችሁ አእምሮ እድገት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያመጣል። ለከፍተኛ ጉዳትም ይዳርጋቸዋል። በመሆኑም መጠጦቹን ከመጠጣት ራሳችሁን አቅቡ” ብለዋል። ቀጥለውም አደገኛ ዕጾችን፣ ለምሳሌ ጫትን በእርግዝና ወቅት መጠቀም ከጽንስ መጨንገፍ ጀምሮ የጽንስ መቀጨጭን ሁሉ እንደሚያስከትል በጥናቶች ተረጋግጧል። ሌሎች አደንዛዥ ዕጾችን መጠቀምም በሆድ ውስጥ እያለ ጭምር ሱሰኛ ሆኖ እንደሚወለድ የሚያሳዩ ጥናቶች አሉ። ለአብነት ሄሮይን፤ ክራማዶንና ሌሎች አደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶችን በእርግዝና ወቅት መጠቀም በቀጥታ በህፃኑ ላይ ሱሰኝነትን እንደሚያስከትል በጥናት ተረጋግጧል። በመሆኑም የትኛውንም ዓይነት አእምሮን የሚለውጥ መድሃኒት፣ የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች፣ ጫት፣ ትምባሆና ሌሎች አደንዛዥ ዕጾችን በእርግዝና ወቅት መጠቀም በጽንስ ላይ ችግር ያስከትላልና ታቀቡ በማለት ደጋግመው ነፍሰ ጡርና ሌሎች ሱስ አስያዥ እፆችን ተጠቃሚ ሴቶች ይመክራሉ።

## ልማዳዊ ድርጊቶች

አቶ ኤሊያስ ካሳይ ከዚሁ ከሱሰኝነት መከላከል ጋር በተያያዘ እየሰራ ያለ ተቋም (መቋሚያ) ዋና ዳይሬክተር ናቸው። የአደገኛ ዕፅ ሱሰኝነት ቅድመ መከላከል ባለሙያ ሲሆኑ “መቋሚያ የሱስ ሳይንስ” የሚል መጽሐፍም ደርሰዋል።

አቶ ኤሊያስ እንደሚሉት በአገራችን አደገኛ አደንዛዥ ዕጾችና የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች፤ እንዲሁም ፊልሞችና የመሳሰሉት መስፋፋት አደንዛዥ ዕጾችና የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች ተጠቃሚ ቁጥር እንዲጨምር እያደረጉ ይገኛሉ። በዚህ ውስጥ ደግሞ ለማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ስነልቦናዊና አእምሯዊ ችግሮች በበለጠ ሰለባ የሚሆኑት በሴትነታቸው ሰፊ ማህበራዊ ኃላፊነት የተጣለባቸው ሴቶች ናቸው።

ሱሰኝነት ሴቷን ብቻ ሳይሆን የምትወልደውን ልጅም ጭምር ይጎዳል። ቀስ በቀስ የቤተሰብን፤ የወዳጅ ዘመድ የሰላምና የተረጋጋ ህይወት ጠንቅም ይሆናል። እንዲሁም በቤተሰብ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያሳድራል። የኢትዮጵያ መድኃኒት ፋብሪካ በ2002 ዓ.ም ያወጣውን፣ በወቅቱ የነበረ የአደገኛ ዕጾች መሸጫ ዋጋን ሪፖርትን ዋቢ አድርገው እንዳብራሩት፣ ግማሽ ሺሻ ለማጨስ 30 ብር፤ ሙሉ ሺሻ ለማጨስ ደግሞ 60 ብር ይጠይቃል። ይህም እንደሚጨስበት ቤትና በተጨማሪ እንደሚወሰደው ሱስ አስያዥ የዕፅ ዓይነት ይለያያል። እንደ ጫትና ሌላም ሱስ አስያዥ ዕፅ ከሺሻው በተጨማሪ ከተወሰደ ደግሞ፤ ክፍያው እስከ ብር 100 እና በላይ ይደርሳል። ከዚህም በተጨማሪ ሌላ ሱስ አስያዥ ዕፅ ሳይጨመር ሺሻን ብቻ በወር አራት ቀን የሚያጨስ ተጠቃሚ በወር በአማካይ ከብር 120 እስከ 240፤ አዘውትሮ የሚጠቀም ደግሞ በትንሹ ከብር 600 እስከ ብር 1000 ያወጣል። ይህም ተጠቃሚው ሴትም ሆነ ወንድ በቤተሰቡ ኑሮ ላይ የኢኮኖሚ መናጋት ያስከትላል። በማጨስ የሚባክነው ገንዘብም እንዲሁ የገቢ መቀነስን ያስከትላል። ተጠቃሚዋ ሴት በምትሆንበት ጊዜ ደግሞ ካላት ሰፊ ኃላፊነት አንፃር ተጽዕኖው በእጅጉ ይገዝፋል። ተቋማቸው ተፅዕኖውን በመቀነስ ችግሩን ከመቅረፍ አኳያ በተለይ ሴቶች ላይ ትኩረት አድርጎ ይሰራል። የገቡት እንዲወጡ፤ ያልገቡት እንዳያገቡ ቅድመ መከላከል ላይ የሚሰራውንም በማሳያነት ያነሳሉ። መጤ ባህል ኩረጃ የሚዘወተርባቸውና አደገኛ አደንዛዥ እጾችን መጠቀም ባህል ያደረጉ አካባቢዎች ከዚህ ልማዳቸው እንዲላቀቁ ለማድረግ ረጅም ጊዜ ቢፈጅም ባህልና ልምዱን ባከበረ መልኩ ሱሰኝነትና ጉዳቱን ነጥሎ የማውጣት ሙከራ እየተደረገ መገኘቱንም አቶ ኤልያስ ያወሳሉ። ለአብነትም በምስራቁ የአገራችን ክፍል ጫት በተዘጋ ቤት ውስጥ፤ እንዲሁም፣ ከኮካ ኮላና ከአልኮል መጠጥ ጋር ሳይሆን እንዲሁ እየተናፈሱ ውጪ ሆነው እንዲቅሙ በማስለመድ ከመቃም ጋር ተያይዞ የሚመጣን ጉዳቱ ለማስቀረት እየተደረገ ያለውን ጥረት ያነሳሉ።

እኛም ከማንኛው ሱስ ነፃ የሆነ ህብረተሰን ይፈጠር ዘንድ በመመኘት ዝግጅታችንን በዚሁ እናጠናቅቃለን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ትናንት ስመሳው ኢትዮጵያ የመረጃ ቋት ነበረ። በእነዚህ ትናንቶች ውስጥ ያለፉት መረጃዎች ዛሬ ላይ የታሪክ ማህደር ነጸብራቆች ሆነው ይታያሉ። ሁሉንም ነገሮች በአዲስ ዘመን ድሮ መስታወት ፊት ቆመን የድሮዋን ኢትዮጵያ ታሪካዊ ምስል እንመለከታለን። በኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄዱ ክስተትና ታሪኮች ሁሉ በአዲስ ዘመን ድሮ ውስጥ ተሰንደው ተቀምጠዋል። እኛም ተገልጦ ከማያልቀው ክምችት ውስጥ የመራረጥናቸውን ጥቂት ጉዳዮች እናካፍላችሁ፡፡ የጋዜጠኞች ማህበር ጉባኤ ስላስተላለፈው ውሳኔ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ደግሞ በአንድ ወቅት አንድ የሆነ ችግር አጋጥሞት ነበር፤ ስለመሆኑ የገጠመው ችግር ምን ይሆን...ውስኪ ያልሆነን ነገር ውስኪ ነው እያሉ ስብዙዎች እያከፋፈሉ ስለነበሩት አጭበርባሪዎች.... እንዲሁም ደግሞ ከመፍትሔ ቢሆንም ገጽ ሳይ-አንዲት ግለሰብ ጓደኛዬ የወሰደውን ድንግልና ውስጂ እያስ ክፉኛ ያስጨንቀኛልና መሳ በሉኝ ያለችበትን አስገራሚ ዘገባ እንደሚከተለው እናስታውሳችሁ።

**የጋዜጠኞች ማህበር ጉባኤ ውሳኔ አሳለፈ**

(ኢ.ዜ.አ)- ክልሎች ከዋናው ማህበራቸው የሚወርድ መመሪያ ሳይጠብቁ በራሳቸው አቅም ሊፈጽሙዋቸው የሚገቡ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል መመሪያ እንዲቀረጽ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር የምክር ቤት ጉባኤ ወሰነ፡፡

ለሁለት ቀናት የቆየው የማህበሩ ምክር ቤት ጉባኤ እሁድ ሲጠናቀቀ ባወጣው መግለጫ እንደጠቆመው፤ ይህንኑ ተግባራዊ የሚያደርግ የማህበራት ጉዳይ ኮሚቴ በማዕከል ተቋቁሞ የግንኙነት መመሪያና አጠቃላይ መርሐ ግብር ይነድፋል፡፡

ጉባኤው ባወጣው ባለ አስር ነጥብ መግለጫው ቀደም ሲል ማዕከሉ ከክልሎች ጋር የነበረው የግንኙነት መስመር በውል ያልታወቀ፣የስራ ክፍሉም በግልጽ ያልተመለከተ እንደነበርና በዚህ ረገድ አያሌ ችግሮች መከሰታቸውን አውስቷል፡፡ (አዲስ ዘመን የካቲት 19 ቀን 1989ዓ/ም)

**አየር መንገድ አሳሳቢ ችግር ውስጥ ነው**

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፎከር ከተባለ የሆላንድ ኩባንያ አምስት አውሮፕላኖችን ለመግዛት ተዋውሎ እንደነበርና በአሁኑ ወቅት ኩባንያው ከስሮ በመዘጋቱ በቀብድ መልክ የተከፈለውን 7 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር / ከ33 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር በላይ/ የማስመለሱ ተግባር አጣዳፊና አሳሳቢ መሆኑን የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ገለጹ፡፡

ዶ/ር አህመድ ቀሎ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ስራ አስኪያጅ በጽ/ቤታቸው ለተገኘው ለፕሬስ ጋዜጠኞች ቡድን በሰጡት መግለጫ፤ አየር መንገዱ ውሉን በሚፈጽምበት ጊዜ ጭምር ፎከር የፋይናንስ ቀውስ ውስጥ እንደገባ ያውቅ እንደነበር ገልጸው፤ ነገር ግን እዚህ ደረጃ ላይ ደርሶ ጨርሶ ይዘጋል ተብሎ እንዳልተገመተ አመልክተዋል፡፡

ዋና ስራ አስኪያጁ እንደገለጹት፤ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ከኩባንያው ለመግዛት የተዋዋለው አምስት አውሮፕላኖች ዋጋ 87 ሚሊዮን ዶላር ነው፡፡ ውሉ ሰፊ ሲሆን የጥገና ማዕከል መስራት፣ 2 ሺ ሰላሳ የሚሆኑ የተለያዩ መለዋወጫዎችን መስራት፣ሥልጠና ማካሄድና የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው፡፡ (አዲስ ዘመን ሚያዚያ 27 ቀን 1988ዓ/ም)

**የመጀመሪያ ዙር የኃይል ማመንጫ ግንባታ እየተካሔደ ነው ተባለ**

(ኢ.ዜ.አ)- የግልገል ጊቤ ሃይደሮ ኤሌክትሪክ ፕሮጀክት የመጀመሪያው ግንባታ ሲጠናቀቅ በአሁኑ ወቅት ስድስት የማመንጫ ጣቢያዎች የሚይዘውን 340 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይል ወደ 480 ከፍ እንደሚያደርግ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክና መብራት ሃይል ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

.....................

እንደ ስራ አስኪያጁ አባባል ከሆነ ፕሮጀክቱን በአዲስ መልክ ለማዋቀር ያስፈለገበት ምክንያት ቀደም ሲል አለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው መንገድ ባለመዋቀሩና ባለፉት አስር አመታትም በተጉዋዳኝ ስራዎች ላይ ብቻ ሲያዘግም በመቆየቱ ነው፡፡

ዓለም አቀፍ ተቀባይነት የሌለው ዓይነቱ አወቃቀርም አስተዳደራዊ በደልንና ሙስናን ለማስወገድ ከማስቻሉም በላይ የጊዜ ብክነትንም እንደሚያስወግድ አስታውቀዋል፡፡

(አዲስ ዘመን ሚያዚያ 27 ቀን 1988ዓ/ም)

**ሐሰተኛ ውስኪ ሲያከፋፍሉ የተገኙ ተያዙ**

የአዲስ አበባ መስተዳድር ፖሊስ ኮሚሽን የተለያዩ የአልኮል መጠጦችን የተወሰነ መጠን ካለው ውስኪ ጋር በመቀላቀል እውነተኛ ውስኪ አስመስለው እየቀመሙ በሽያጭ አከፋፍለዋል ያላቸውን ሶስት ሰዎች ሰሞኑን መያዙን አስታወቀ፡፡

በወረዳ 10 ቀበሌ 05 ውስጥ የግለሰብ ቤት ተከራይተው ይህንኑ ሐሰተኛ ውስኪ የሚሰሩት ሰዎች በቁጥጥር ስር ሊውሉ የቻሉት ለዞን አራት ፖሊስ ጽሕፈት ቤት በደረሰው የሰዎች ጥቆማ መሠረት እንደሆነ የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የመቶ አለቃ ያሬድ መለሰ ገልጠዋል፡፡

.....................

በወንጀሉ ተሳታፊ የሆኑት ግለሰቦች ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ በዚህ ስራ ከተሰማሩ ሁለት ዓመት እንደሚሆናቸውና ይህንንም ምርታቸውን የሚያከፋፍሉት እዚህ አዲስ አበባ ለሚገኙ ደንበኞቻቸቸው መሆኑን ገልጠዋል፡፡

(አዲስ ዘመን ሚያዚያ 27 ቀን 1988ዓ/ም)

**ጓደኛዬ የወሰደውን ድንግልና ውስጂ እያስ ክፉኛ ያስጨንቀኛል**

ጥያቄ-ለኔ የመጀመሪያ የምለው ጓደኛዬ ጋር ከተዋወቅን ሁለት አመት ሊሆነን ነው። በእርግጥ ለመተዋወቅ ብዙ ጊዜ ጨርሶብናል። በዚህ ጊዜም “የሚዋደዱና የሚተማመኑ ጓደኛሞች ላይ ላዩን ይሄዳሉ “ ስላለኝም አምኜው ሄድንበት። በዚህም ጉዞ ያመኝ ነበር። በዚህ መልኩ 6ወር ከቆየን በኋላ ልጃገረድ አይደለሽም ከሚልበት ደረጃ ላይ ደረስን። እኔ እንኳንስ ለዚህ የሚያበቃኝን ስሞኛል የምለው ጓደኛ አነበረኝም። በጣም የባሰብኝ ደግሞ በትንሽ ነገር የተነሳ የሚያወርድብኝ የስድብ ናዳ ነው። ይልቁንም “አንቺ እኮ እንደዚ ነሽ፣ እኔ ሐጻን ወይስ ምንም የማላውቅ መሐይም መሰልኩሽ? ልታታልይኝ ነው? ያልተነካ ነው እንጂ የጠፋው ትርፍራፊማ ሞልቷል“ እያለ በጠበጠኝ። ከዚህ የተነሳ በጣም ተጨነቅሁ።

**ሰላም**

**(አዲስ ዘመን ሚያዚያ 16 ቀን 1988ዓ/ም)**

# ዓለም አቀፍ

## የአይ ኤስ መሪ አልቁረይሺ መገደሉን የቱርኩ ፕሬዚዳንት ኤርዶዋን ተናገሩ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሶሪያ የኢስላሚክስ ስቴት (አይ ኤስ) መሪ አልቁረይሺ በቱርክ ኃይሎች መገደሉን የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ረሲብ ጣይብ ኤርዶዋን ተናገሩ።

አቡ ሑሴይን አልቁረይሺ በሚል ሙሉ ስሙ የሚታወቀው የአይ ኤስ መሪ መገደሉን ኤርዶዋን ይፋ ያደረጉት ለቲአርቲ ሚዲያ ነው።

ይህን እርምጃ የወሰዱት ደግሞ የቱርክ የስለላ እና ደኅንነት አባላት መሆናቸውን ፕሬዚዳንቱ ጨምረው ገልጸዋል።

ኢስላሚክ ስቴት (አይ ኤስ) እስከ አሁን ዜናውን አላስተባበለም። ቢቢሲ የኤርዶዋንን ቃል ከሌላ ገለልተኛ አካል አላጣራም።

የቱርክ የስለላ እና ደኅንነት መሥሪያ ቤት ቁራይሺን ረዘም ላለ ጊዜ ሲከታተለው እንደነበር ኤርዶዋን አብራርተዋል። ከአሸባሪዎች ጋር የምናደርገው ትግል አሁንም ይቀጥላል ሲሉም ተናግረዋል።

ሮይተርስ ያነጋገራቸው በሶሪያ የሚገኙ ምንጮች በበኩላቸው ይህ ኦፕሬሽን የተደረገው ከቱርክ ድንበር



አቅራቢያ ጃንዳሪስ በምትባል ትንሽ ከተማ ውስጥ መሆኑን ተናግረዋል።

ባለፈው ኅዳር የጂሃዲስት ቡድኑ የዚያን ጊዜ መሪው አቡ አል ሐሳን አል ሐሺሚ መገደልን አረጋግጦ ነበር።

አሜሪካ አል ሐሳን አል ሐሺሚ ባለፈው ጥቅምት ወር አጋማሽ ላይ በሶሪያ ነፃ አውጪ ሠራዊት መገደሉን ይፋ ካደረገች በኋላ ነበር ቡድኑ ይህንኑ ያረጋገጠው።

ጆ ባይደን ይህን በማስመልከት በወቅቱ ባስተላለፉት መልዕክት «የዓለም ትልቁ የሽብር ስጋት ተገድሏል» ብለው ነበር።

አሁን የተገደለው አልቁራይሺ የአል ሐሺሚን መገደል ተከትሎ የኢስላሚክ ስቴት መሪ ሆኖ የተሾመ ነው።

አይ ኤስ ከዓመታት በፊት 88 ሺህ ስኩዌር ኪሎ ሜትር የሚሆን ሰፊ ግዛት ተቆጣጥሮ እስላማዊ መንግሥት (ካሊፌት) መስርቶ ማስተዳደር ጀምሮ ነበር።

ይህም ከሰሜን ምሥራቅ ሶሪያ እስከ ሰሜን ኢራቅ የሚዘረጋ እና ከ8 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የሚኖርበት አካባቢ ነበር።

በአውሮፓውያኑ 2019 በተደረገ ኦፕሬሽን ቡድኑ ክፉኛ ተሸንፎ ተበታትኖ ቆይቷል። አሁን በሶሪያ እና በኢራቅ እስከ 10 ሺህ የሚደርሱ ተዋጊዎች እንዳለው ይነገራል።

ለአይ ኤስ ድጋፋቸውን የሚሰጡ ቡድኖች ግን በአፍጋኒስታን፣ በሶማሊያ እና በቻድ አሁንም ድረስ አሉ።

## ሕንድ ውስጥ በመርዘኛ ጋዝ ምክንያት ቢያንስ 11 ሰዎች ሞቱ



በጋዜጣው ሪፖርተር

በሰሜናዊ ሕንድ ውስጥ ባፈተለከ መርዘኛ ጋዝ ምክንያት ቢያንስ የ11 ሰዎች ሕይወት መጥፋቱ ተዘገበ።

በሕንድ ፑንጃብ ግዛት ውስጥ ባለችው የወደብ ከተማዋ ሉድሃይና ውስጥ በደረሰው በዚህ አደጋ ከሞቱት ሰዎች ውስጥ ሴቶችና ሕፃናት ይገኙበታል። በተጨማሪም በርካታ ሰዎች በቤታቸው ውስጥ እራሳቸውን ስተው ተገኝተዋል። አራት ሰዎች በሆስፒታል ውስጥ ሕክምና እየተደረገላቸው ነው።

ብዙ ሰዎች የመተንፈስ ችግር እንዳጋጠማቸው ከተነገረ በኋላ አደጋው የደረሰበት አካባቢ እንዲዘጋ እና ነዋሪዎች እንዲወጡ ተደርጓል።

የመርዘኛ ጋዙ ምንጭ ምን እንደሆነ የታወቀ ነገር ባይኖርም፣ አንድ ባለሥልጣን ግን ከመሬት በታች ካለ ቱቦ ውስጥ አፈትልኮ የወጣ ሊሆን ይችላል ብለዋል።

የሉድሃይን ከተማ ምክትል አስተዳዳሪ ሱራብሂ ማሊክን ፕሬስ ትረስት ኢንዲያ ለተባለው ዜና ወኪል እንደተናገሩት፣ በከተማዋ ውስጥ ካሉ ጉድጓዶች ናሙናዎችን ወስደን እንመረምራለን። በጉድጓዶች ውስጥ ሜቱን የተባለው ኬሚካል ሊፈጠር ይችላል ብለዋል።

የሕንድ ብሔራዊ የአደጋ ምላሽ ግብረ ኃይል ቡድን ምርመራ እንዲያደርግ ወደ ስፍራው መላኩን ቢቢሲ ዘግቧል።

ከሦስት ኣመት በፊት በአንድራ ፕራዴሽ ግዛት ውስጥ በምትገኘው ቪሳኻፓትናም በተባለችው ከተማ ከነበረ የኬሚካል ፋብሪካ ባፈተለከ ጋዝ ምክንያት ቢያንስ 12 ሰዎች መሞታቸው ይታወሳል።

# ስፖርት

## ስፖርት ለሁሉም የማህበረሰብ ባህል እንዲሆን የተጀመረው ውጥን

**ብርሃን ፈይሳ**

የዓለም ጤና ድርጅት የአካል ብቃት እንቅስቃሴን አዘውትሮ ማድረግ ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ሊታደግ እንደሚችል ያስገነዝባል። በኢትዮጵያም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች 51 በመቶ እንደተሻገሩ መረጃዎች ያመላክታሉ። ከእነዚህ መካከል ደግሞ 21 ከመቶ የሚሆኑት ተጠቂዎች ወጣቶች ሲሆኑ፤ በርካታ ቁጥር ያላቸው ደግሞ ለሞት ይዳረጋሉ። ይህንን ችግር ለመፍታትም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ማህበረሰቡ የሚሳተፍበትን የስፖርት ለሁሉም መርሃ ግብር ላይ አተኩሮ በመስራት ላይ ይገኛል።

በዚህ ወቅት በስፖርቱ ዘርፍ በተለየ ሁኔታ ትኩረት የተሰጠው ለስፖርት ለሁሉም ልማት መሆኑን በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ልማት መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ በቀለ ያስረዳሉ። ለዚህም ምክንያት የሆነው ህብረተሰቡን በስፖርቱ በማሳተፍ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማውና ተጠቃሚ እንዲሆን ነው። ነገር ግን በዚህ እንቅስቃሴ ተተኪ በመሆን በአህጉርና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ሀገርን የሚያስጠሩ ስፖርተኞችን ማፍራትም ሌላኛው ዓላማው ነው። የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ የሚያጠነጥነውም ህብረተሰቡን በስፖርት ተሳታፊ ማድረግ በሚለው ሃሳብ ላይ በመሆኑ ይህንኑ ሊደግፍ ይችላል።

የማህበረሰብ አቀፍ ስፖርት በአዲሱ የስፖርት ሪፎርም ከዚህ ቀደም ያልተሰራበት በሚል ለይቶ ተቀምጧል። በዚህም መሰረትም በዚህ ዓመት በእንቅስቃሴው ተሳታፊ ለማድረግ የታቀደው 480ሺ የሚሆን የማህበረሰብ አካል በሚኖርበት አካባቢ፣ 280ሺ የሚሆነው ደግሞ በሚሰራበት አካባቢ ተሳታፊ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።


አዘውትሮ አካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ጤናን መጠበቅ ባህል መሆን ይገባል፣

በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ወደ 30 ሚሊዮን የሚጠጉ ሲሆን፤ 24 ሚሊዮን የሚሆኑትንም በስፖርት ለሁሉም እንቅስቃሴው ለማካተት እየተሰራ ነው። በዚህም ከአጠቃላይ ህብረተሰብ 20 ከመቶ ለመሸፈን ታስቦ ከ19 በመቶ በላይ የሚሆነው መሳካቱን ቡድን መሪው ያስረዳሉ።

ከዚህ ቀደም በተካሄደ የስፖርት ለሁሉም ብሄራዊ የአንድ ሰዓት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መርሃ ግብርም፤ በሁሉም ክልል 5ነጥብ4 ሚሊዮን ህዝብ ተሳታፊ መሆኑ ተረጋግጧል። ሁሉም ጋር የነበረው እንቅስቃሴ ተመሳሳይ ባይሆንም እንደ አዲስ አበባ እና ደቡብ ክልሎች ባሉት የተሻለ ሁኔታ ነበር። ችግሩ በተለይ ጎልቶ በሚታይበት አዲስ አበባ ያለው ተሞክሮ አመርቂ የሚባል ሲሆን፤ ህብረተሰቡ ግንዛቤው ስላለው የመርሃ ግብሩን መካሄድ ሳይጠብቅ አካል ብቃት እንቅስቃሴ እንደሚያደርግም ታይቷል። በድሬዳዋ፣ ሃረሪ እና የኦሮሚያ ክልል አንዳንድ ከተሞች ያለው እንቅስቃሴም አበረታች የሚባል ነው።

ነገር ግን በትምህርት ቤቶች ውስጥ ንቅናቄውን በሚፈለገው ልክ ማስኬድ አልተቻለም። በተለይ ባንዲራ መውጫና መውረጃ ላይ በየቀኑ ከ20-30 ደቂቃ ወስደው እንዲሰሩ ለማድረግ ቢሞከርም እንደታቀደው አልሄደም። በአንጻራዊነት በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ክልል ያለው የተሻለ ቢሆንም፤ እንደአጠቃላይ ሲታይ ስኬታማ ሊሆን አልቻለም። ለዚህም እንዲረዳ ሁለት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ተዘጋጅተዋል፤ ይሁንና አሁንም ለውጥ እየታየበት አይደለም።

ሁለተኛው ሀገር አቀፍ የአንድ ሰዓት ስፖርት ለሁሉም መርሃ ግብርም ከትናንት በስቲያ ተካሂዷል። ይህም ህብረተሰቡ በዕለት ተዕለት ህይወቱ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ለአንድ ሰዓት ማድረግ ልምድ እንዲሆነው ያስችላል። ሰራተኞችን በሚመለከትም 28 የሚሆኑ የፌዴራል መስሪያ ቤቶችን ያካተተ የስፖርት ውድድር በተያዘው ወር አጋማሽ ማካሄድ ተችሏል። ውድድሩ የራሱ ህግና ደንብ ተዘጋጅቶለት በ7 የስፖርት ዓይነቶች ነበር የተካሄደው። በቀጣይም አንደኛው ሀገር አቀፍ የሰራተኞች ስፖርት ለሁሉም ፌስቲቫልን በአማራ ክልል ደሴ ከተማ ላይ ለማካሄድ ታቅዷል። በዚህም ህብረተሰቡን በውድድርም ሆነ በመዝናኛ መልክ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተሳታፊ በመሆን ጤናውን መጠበቅ ይችላል ተብሎ ታስቧል። በሂደትም ንቁ፣ ጠንካራና አሸናፊ ማህበረሰብን መፍጠር የሚለውን ግብ መምታት ይቻላል የሚል እምነት አለ።

መንግስት ለዚህ እንቅስቃሴ ትልቅ ትኩረት እንደመስጠቱ ከፍተኛ በጀትም ተመድቦለታል። ከዚህ ባሻገር ስመጥር አትሌቶችንና ስፖርተኞችን በዚህ የልማት ስራ በማሳተፍም ማህበረሰቡን ለማነቃነቅም ይሰራል። ይህ ስራ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑንም ስራ አስፈጻሚው አረጋግጠዋል።

## ከሰላሌ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎትን በተግባር

**ታምራት ተስፋዬ**

የከፍተኛ ትምህርት ተማት ከመማር ማስተማር እና ምርምር ሥራዎች ባሻገር በማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት የላቀ ተልዕኮና ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል። የሠላሌ ዩኒቨርሲቲም የተሰጡትን ሀገራዊ ተግባርና ኃላፊነት በመወጣት ሂደት በተለይ በማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ችግሮችን የሚያቀሉ ለሁለንተናዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ያላቸው የጥናት፣ የምርምርና የማማከርና የድጋፍ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።እያከናወነም ይገኛል።

የዩኒቨርሲቲው የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር እሸቱ ወንድሙ እንደሚገልፁት፣ አንድ ዩኒቨርሲቲው ሲ ቋቋም ሶስት ታላላቅ ዓላማዎችን አንግቦ ነው። አንደኛው የመማር ማስተማር ሥራ ነው። ሁለተኛው ችግር ፈቺ ምርምሮችና ማድረግ ሲሆን ሦስተኛው የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ተሳትፎ ነው።

ሰላሌ ዩኒቨርስቲም ከመማር ማስተማርና ምርምር ሥራዎች ጎን ለጎን የአካባቢውን ማህበረሰብ ህይወት ለማሻሻል በሚያግዙ የተለያዩ ተግባራትን በመከወን ላይ ይገኛል። በዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች ሲሠሩ ፍላጎትን በሚገባ በማወቅ፣ በቅንጅት፣ ተጽኖናና ለውጥ ሊያመጡ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሁም ተገቢ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ አካባቢን ከመቀየር አልፎ ህዝብንና ሀገርን ተጠቃሚ ማድረግ በሚያስችል መልኩ ነው። ዩኒቨርሲቲው በዚህ ረገድ የተለያዩ አገልግሎቶች ላይ አሻራ እያሳረፈ ይገኛል።

ለአብነትም የሁለትዮሽ ግንኙነቶችን በማጠናከር ከተለያዩ የውጭ አገራት ጋር በመፃፃፍ ሁለት ኮንቴነር መድህኒትና የህክምና ቁሳቁሶችን በማስመጣት አስር ለሚሆኑ የህክምና ተቋማት እንዲከፋፈል አድርጓል። ገብረ ጉራቻ፣ ሙከጡሪ፣ ፊቼ ፣ መርሃቤቴ እናት ሆስፒታል ፣ ጉንዶ መስቀል ፣ጫንጮ፣ ለአዲስ አበባ ከተማ በተለይ ጳውሎስ ፣አለርትና ሚኒሊክ እንዲሁም አማኑኤል የተለያዩ መድሃኒቶችና የህክምና መስጫ ቁሳቁሶችን ተደራሽ የሆነባቸው ሆስፒታሎች ናቸው።በዚህ ተግባርም የህክምና የተቋማቱን ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡንም ችግሮች ማቃለል ተችሏል።

ተመሳሳይ የውጭ ግንኙነት ትስስር በመፍጠር ሁለት ኮንቴነር ሙሉ መፅሃፍን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት ከአንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ለሚገኙ ሶስት መቶ ትምህርት ቤቶች አከፋፍሏል። በዚህም በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የትምህርት ቤቶቹ የመማር ማስተማር ፈተና የነበረውን የመፅሃፍ እጥረቶች በእጅጉ በማቃለል ተቋማዊ ሃላፊነቱን ተወጥቷል።፡

በሌላ በኩል የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ በማሰባሰብ በወር አንድ ጊዜ የበጎ አድራጎት ሥራ የአካባቢው ማህበረሰብ በተለይም አቅመ ደካማ እና ችግረኛ የሆኑት ፍትህ እንዲያገኙ ከማድረግ አንፃር ዘርፈ ብዙ ተግባራት ማከናወን ተችላል። በተለይ በገንዘብ እጦት በእውቀት ማነስና ባለመማር ምክንያት ፍትህ እንዳይጓደል ነፃ የህግ አገልግሎት በተለያዩ ወረዳዎች ላይ እየሰጠም ይገኛል።

ዩኒቨርሲቲው በየዓመቱ ከሶስት መቶ እስከ 600 ለሚሆኑ ግለሰቦች መሰል ነፃ የሕግ አገልግሎት ድጋፍ የሚሠጥ ሲሆን ይሕ የሚከናወነውም በተለያየ መልኩ ነው። አንደኛው ማመልከቻዎችን በመፃፍ፣ጥብቅና በመቆም፣ የሕግ ግንዛቤ እንዲያገኙ በማድረግ እንዲሁም በማዕከሉ ላይ ስልጠና በመስጠት ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል።


ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር እሸቱ ወንድሙ

በቦረና ከተከሰተው ድርቅ ጋር በተያያዘ ጠቅላላው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተማሪዎች መምህራን የአስተዳደር ሠራተኞች፣ በራሳቸው ፈቃድ የድጋፉ ተካፋይ መሆን አለብን በሚል ለወገናቸው ከአራት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ብር በላይ የሆነ የአይነት ድጋፍ አድርገዋል።

ዩኒቨርሲቲው በፌደራል መንግሥት ደረጃ አንባቢና አምራች ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚደረገውን አገራዊ ጥረት እያገዘ ይገኛል።ለአብነትም የቅርብ ጊዜ ህትመት የሆኑና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ከ18 ሺ በላይ መጻሕፍትን ለአብርሆት ቤተ -መጻሕፍ አበርክቷል።

ከዩኒቨርሲቲው ዘንድ ያሉ እውቀቶች ለማህበረሰቡ እንዲወርድ ለማድረግ ስልጠናዎችን በየዘርፉ ለተለያዩ ባለሙያዎች እየሰጠም ይገኛል።ወላጅ አልባና አቅም ደካማ ብሎም ችግረኛ ለሆኑ ቤተሰቦች በዘንድሮ አመት ብቻ 2ሺ ለሚሆኑ ተማሪዎች አጠቃላይ የትምህርት ግብዓቶችን በመቻል ትምህርታቸው እንዳያቋርጡ ድጋፍ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

የአካባቢውን ማሕበረሰብ ከማገዝ አንፃር በተለይም አቅም ደካማ ለሆኑ ሰዎች የጤና መድህን ዋስትና እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ ሠርቷል። በዘንድሮው ዓመት ብቻ ለ108 ሰዎች መሰል እገዛ አድርጓል። ፅዱና አረንጋዴ ከተማን እውን በማድረግ ረገድ የፍቼ ከተማን በማስዋብ ተሳትፎም እያደረገ ይገኛል።

የተቀናጀ የአካባቢ ጥበቃና የተፋሰስ ልማት ሥራዎች፣ የችግኝ ማፍላትና ሥርጭት፣በግብርናው ዘርፍ ላይ የተሻሻሉ ና አዳዲስ ዝርያዎችን የማፍለቅና ለአርሶ አደሩ ተደራሽ በማድረግ ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ በስፋት እየሰራ ይገኛል። በዚህም በርካቶችን ተጠቃሚ በመሆን ላይ ናቸው።

ዶክተር እሸቱ እንደሚያስገነዝቡትም፣ እነዚህ ተሳትፎዎች ለአብነት ይጠቀሱ እንጂ ዩኒቨርሲቲው ለሕብረተሰብ ዘላቂ ለውጥ እውን መሆን በጥናትና ምርምር ላይ የተመሰረተ የማህበረሰብ አገልግሎት ላይ የሚያከናውናቸው ሥራዎች በርካታ ናቸው። ዩኒቨርሲቲው ለማህበረሰብ አገልግሎት በሚሠጠው ትኩረት ከጊዜ ወደ ጊዜ በተደራሽነቱ እያደገ የህብረተሰቡ ተጠቃሚነትም እየጎለበተ መጥቷል።

በዚህ ሁሉ የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎትና የበጎ ምግባር ተሳትፎ ውስጥ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባላት ደከመኝ፣ሰለቸኝ ፣አቅም አጣን ሳይሉ ምንጊዜም ተባባሪነታቸውን እያስመለከቱም ይገኛሉ። ዩኒቨርሲቲው በቀጣይም የአገርንም ሆነ የህዝብን ችግር ለማቃለል ብሎም ለማጥፋት በመሰል ማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶች ይበልጥ ተሳታፊ መሆኑን ይቀጥላል።